

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና (በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት)

በ

ወንዱ ፀጋ

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሐ- ግብር

አማርኛን ለማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ወንዱ ፀጋ

የጥናቱ አማካሪ

ተስፋዬ ሸዋዬ

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋ ጥናት ፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጂ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና (በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል መምህራን ተተኪሪነት)

በ

ወንዱ ፀጋ

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

አማካሪ ስም ————————ፊርማ ———— ቀን

የውስጥ ፈታኝ ————————ፊርማ ———— ቀን

የውጭ ፈታኝ ————————ፊርማ ———— ቀን

በአጥኚው የቀረበ ማረጋገጫ

ይህ ጥናት ‹‹አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና›› በሚል አርዕስት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሐ- ግብር የቀረበው ጥናት የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ————————ፊርማ፡- ————————ቀን፡- ————

ምስጋና

በመጀመሪያ በመሰናክሎች መሃል እና ተስፋን በሚፈታተነው የህይወት ጉዞ ሁሉ እስካሁን ለጠበቀኝ ፈጣሪዬ ልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ይመስገን።

በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱን በማየትና የማስተካከያ እርማቶችን በመስጠት እገዛና አስተዋፅኦ ላደረጉልኝ ውድ አማካሪዬ፣ ለተስፋዬ ሸዋዬ ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። ሁሉ የእርሱ የሆነ ቸሩ እግዚአብሔር እድሜና ጤና አብዝቶ ይስጥልኝ።

በመጨረሻም ትምህርቴን ለተከታተልሁበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለጢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ለቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ይድረስልኝ።

አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍልአራት አማርኛ ቋንቋ መምህራን ትኩረቱን በማድረግ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ መተንተን ነው። የዓላማውን ውጤት ለማስገኘትም ቃለ መጠይቅና ምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግለዋል። በዚህም አጥኚው ተምህርት ቤትን በአመቺ(የግኝት) ናሙና፣ የክፍል ደረጃን በወሳኝ ናሙና ፣ መምህራንን በጠቅላይ ንሙና ዘዴ መርጧል።በአራት ተተኪሪ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ በመገኘት ለአራት መማሪያ ክፍሎች ለእያንዳንዱ ሁለት ሁለት ምልከታ በማድረግና ለአራት መምህራን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በእነዚህ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው ውጤታቸው ተግምግሟል። ከጥናቱ ዓላማ በመነሳት በሚከተለው መልኩ ጥናቱን በማጠቃለል ማቅረብ ተችሏል። መምህራን የማብራራትና መተርጎም፣ መተንበይና መገመት፣ ጥያቄ የመጠየቅ እና የማጠቃለል ብልሃቶችን እየቀያየሩ ለመጠቀም እንደሚሞክሩ ነው ከቃለ መጠይቁ መረዳት የተቻለው። አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍን ክሂሎችን አቀናጅቶ መስጠት ግን የሁለት ክሂሎችን ችሎታ እንደሚያጎናጽፍ ጥናቱ አረጋግጧል። በመሆኑም ለተማሪዎች ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ አንብቦ መረዳትና መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር ክሂሎች እየተቀናጁ እንዲማሩ እንድማሩ ቢደረግ የሚል አቅጣጫ ጥናቱ አስቀምጧል። እንዲሁም የማስተማሪያ ስልቶችን እየቀያየሩ መጠቀም ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ እንደሆነ ጥናቱ የመላክታል።ስለዚህ መምህራን አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ሲያስተምሩ በየትኛው ስልት ማቅረብ እንዳለባቸው ወስነው መቅረብ አለባቸው። ከቀረቡት የጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም ቀጥለው የሚቀርቡት የመፍትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል። መምህራን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት በሚያቀርቡበት ወቅት በቅንጅት የሚቀርቡበትን ዓላማ በመናገር ቢጀምሩ፣ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ሲስተምሩ የማስተማሪያ ዘዴያቸውንና የአቀራረብ ስልታቸውን ከማስተማራቸው በፊት ወስነው ቢቀርቡ፤ መምህራን የማብራራትና መተርጎም፣ መተንበይና መገመት፣ ጥያቄ የመጠየቅ እና የማጠቃለል ብልሃቶችን እየቀያየሩ ለመጠቀም እንደሚጠቀሙ ከጥናቱ ውጤት መረዳት ይቻላል። ስለዙህ ክሂሎችን በተናጠል ከማስተማር ልምድ ወጥተው አንብቦ መረዳትንና መጻፍን አቀናጅተው ቢያሰተምሩ በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሁለት ክሂሎችን በማስተማር የአንብቦ መረዳትና መፃፍ ችሎታዎችንና ተግባቦቶችን ለተማሪዎች የሚያጎናጽፍ መሆኑን ይህ ጥናት ያሳያል።

ማውጫ

ይዘት

ገጽ

አጠቃሎ (Abstract) ii

ማውጫ iii

ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 3

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች 4

1.3.1 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ 4

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች 4

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ 4

1.5 የጥናቱ ወሰን 5

1.6 የጥናቱ ውስንነት 5

ምዕራፍ ሁለት 6

ክለሳ ድርሳን 6

2.1 የቋንቋ ክሂሎች ምንነት 6

2.2 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅት ምንነት 7

2.3. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ ዘዴዎች 8

2.4.የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ ጠቀሜታ ፡ 8

2.5 የአንብቦ መረዳት ምንነት 9

2.5 .1 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት 10

2.5.2 አንብቦ መረዳትን የማስተማር ደረጃዎች 11

2.5.3 የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ 13
2.6 የመጻፍ ክሂል ምንነት 13
2.6.1 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት 14
2.6.2 የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች 15
2.7 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር 18
2.7.1 የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሒል ቅንጅት አስፈላጊነት 19
2.7.2 የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሒሎችን ለማዳበር የሚረዱ ብልሐቶች 19
2.8 የቀደምት ስራዎች ቅኝት 21
ምዕራፍ ሦስት 23
የአጠናን ዘዴ 23
3.1 የጥናቱ ንድፍ 23
3.2.የናሙና አመራረጥ 23
3.2.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ 23
3.2.2 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ 23
3.2.3 የመምህራን አመራረጥ 23
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 24
3.3.1 ምልከታ 24
3.3.2 ቃለ መጠይቅ 24
3.4 የመረጃ ትንተና ዘዴ 24
ምዕራፍ አራት 25
የመረጃ ትንተና 25
4.1 ከቃለ- መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና 25
4.2 ከመምህራን ምልከታ የተገኘ ውጤት ትንተና 30

4.2.1 አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና 30
4.2.2 አንብቦ ስለመረዳትና ስለመፃፍ ክሂል አካታችነት የተገኘ መረጃ ትንተና 31
ምዕራፍ አምስት 37
ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳብ 37
5.1. ማጠቃለያ 37
5.2 የመፍትሔ ሃሳብ 38
ዋቢ መጽሐፍት 39
አባሪ አንድ፡- የመምህራን ቃለ_መጠይቅ 42
አባሪ ሁለት፡- መምህራንን ምልከታ ማድረጊያ 43
አባሪ ሶስት ፡-የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር 44

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ[i]

በዚህ ክፍል የቋንቋ ክሂሎች ምንነት፣የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ፣ዓላማ ፣አስፈላጊነትና ወሰን፣ የሚሉት ርዕሶች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቀርበዋል።

1.1.የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የመጻፍ፣ የማንበብ፣ የማዳመጥና የመናገር አራቱን የቋንቋ ክሂሎችበዋናነት ማዳበር ነው። የክሂሎቹ መዳበር ግብ ደግሞ ውጤታማ ተግባቦትን መፍጠር ነው። ከአራቱ ክሂሎች መካከል ማንበብ የመቀበያ ክሂል፤ መፃፍ ደግሞ የአፍልቆት ክሂል ተብሎው ቢገለጹም በመተላለፊያ መንገዳቸው ሁለቱም ጽሁፋዊ ክሂሎች ናቸው። የማንበብ ክሂል ለአፈ ፈትም ሆነ ለኢ- አፈፈት በትምህርት ቤት የሚያገኙት ክሂል ሲሆን፣ እንደ ማዳመጥ ሁሉ የመቀበያ ክሂልም ነው። ማንበብ ለመፃፍ የሚሆኑ ግብዓቶች የሚቀሰሙበት ክሂል ነው። የማንበብ ክሂል ዋነኛ ዓላማ የፅሁፎችን መልዕክት የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው። Nuttal (1982) እንደገለጹት የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ ተማሪዎች እንደሚያነቡበት ዓላማና የፅሁፍ ዓይነት የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ተጠቅመው እንዲያነቡ ማስቻል፣ አንድ አረፍተነገር በተለያየ አውድ ውሰጥ የተለያዩ መልዕክቶች ሊኖሩት እንደሚችል ማስረዳት ነው ይላሉ።

እንደ Grant (1987)፣ Cunningsworth (1995) እና Richads (2001) ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች በሚመማሩት ቋንቋ በቂ እውቀት እንዲጨብጡ ከማሰቻላቸውም በላይ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች ችሎታ በማመጎልበት ተግባቦትን ማስፋፋት ነው ። ለዚህ ደግሞ የትምህርት መሳሪያዎች ጉልህ ድርሻ አላቸው።

ከላይ ከቀረቡት ምሁራን ሃሳብ መገንዘብ የተቻለው የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች የቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸውና የቋንቋ እውቀት ችሎታቸው የዳበረ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን ለዚህም የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ነው።

‹‹የቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች የሚባሉት ለቋንቋ ትምህርት አገልግሎት የሚውሉና ለአንድ የተወሰነ ክፍል እንዲያገለግሉ ተማሪዎች ሊያገኙ የሚችሉትን እውቀት ሊኖራቸው መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁ ናቸው›› በማለት ተስፋዬ (1981, 89) ይገልጻሉ፡፡

ከቀረበው ሃሳብ መገንዘብ የተቻለው የቋንቋን ክሂሎች ወይም ቋንቋን ለማስተማር የቋንቋ ማስተማሪያ መፃፍት የሚሰናዱ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ሌላ ዓላማ ወይም አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን የምሁራኑ ሃሳብ ያስረዳል፡፡

Richard and Rodgers (1986, 25) በበኩላቸው የቋንቋ ማስተማሪያ መጻህፍት መማር ማስተማር ዘዴ የሚቆጣጠሩ፣ የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት የሚያሳዩ፣ ልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በምሳሌ በማስደገፍ የሚተነትኑ፣ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባሮችን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲሰሩ የሚያነሳሱና በጠቅላላው የቋንቋ ትምህርቱን አካሔድ የሚመሩ ናቸው።ለዚህም በጥንቃቄና በትኩረት ሊዘጋጁ እንደሚገባ ገልጸዋል።የቋንቋ ትምህርት ሲታሰብ ልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች አይቀሬ ናቸው። ይኸውም እንደየ ትምህርቱ ትኩረት እንዲሁም በዚያን ጊዜ እንደነበረው ስለ ቋንቋ ያለው ግንዛቤና አመለካከት ልዩ ልዩ የማስተማሪያ ስልቶች በበርካታ ምሁራን ሲቀርቡ ይታያሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት በመጠቀም ማስተማር የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት በእጅጉ ውጤታማ እንድሆን ያግዛል (Little Wood 1981, 93)::

የቀረበው ሃስብ ላይ መገንዘብ የተቻለው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለመማር ማስተማር ክንውን መረጃ ሰጭ በመሆናቸው ሲዘጋጁ ጥንቃቄን የሚፈልጉ፣ የማስተማሪያ ስነ- ዘዴዎችንና ስልቶችን ያገናዘቡ መሆናቸውን የሚያስረዱ መሆናቸውን ነው፡፡

ተማሪዎች እየተማሩት ያለውን የቋንቋ ችሎታ እንድያጎለብቱ ለማማስቻል በሚገባ የተከናወኑ የትምህርት እቅዶች ያስፈልጋሉ።ለዚህም የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት በመጠቀም በሚገባ ማስተማር የሚቻልበትን መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል።የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማዳበር በቋንቋ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ ጉዳዮች ዋና ዋና ትኩረቶች መካከል ዋናው ነው።በመሆኑም የቋንቋ ክሂሎች በሚስማሙበት መመንገድ በአይነት በአይነት ተከፍለው በቅንጅት ለተማሪው መቅረብ እንደሚገባቸው(Cunningsworth 1995, 74) ገልጸዋል::

የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በእቅድ የሚመራ፣ የራሱ የሆነ አቀራረብ ያለውና የአቀራረቡን ስልት መርጦ መጠቀም የሚጠይቅ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የቋንቋ ክሂሎችን ማጎልበትና ማዳበር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚነደፉት ዋና ዋና አላማዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ከተወሰኑ ጊዜያት ጀምሮ እነዚህን ክሂሎች በቅንጅት መጠቀም ላይ ልዩና ጽኑ እይታ እየተሰጠው እንደሆነ (Byrne 1981, 107) አብራርተዋል።

የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት በመጠቀም ማስተማር ሲባል ትምህርቱ ሲቀርብ የአንዱን ክሂል ከሌላው ተያያዥነት ያለው ክሂል ጋር አሰደግፎ በማቅረብ ማስተማርን እንደሚመለከት (Byrne 1981, 108) እና (McDonugh and Shaw 1992, 201)ይገልጻሉ።

ከላይ የቀረበው ብያኔ የሚያስረዳው የአንብቦ መረዳትና መፃፍ ክሂሎች ትስስር ወይም ቁርኝት ያላቸው መሆኑን የሚገልፅ ነው።

በተጨማሪም በሁለቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዳለና በቅንጅት ቢቀርቡ መልካም እንደሆነ Harp, et al. (1996) እና Ruddel (1997)ገልጸዋል።

ይህ ደጋፊ ሃሳብም ከላይ እንደቀረበው ሁሉ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ትስስር ያላቸው ስለሆነ በውህደት መቅረብ እንደሚችሉ ነው።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት ተኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጂታዊ አቀራረብ ትንትና ምን እንደሚመስል መተንተን ላይ ሲሆን አጥኚው ይህ ጥናት የመረጠበት ምክንያት በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ በጢያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት በሚሰራበት ወቅት በሚደረገው የመምህራን የእርስ በርስ የክፍል ውስጥ ምልከታ ላይ እንዳስተዋለው አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ የማቅረብ ችግሮች በማየቱ ነው። በዚህም መሰረት በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ በጢያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን የአንብቦ መረዳትና መፃፍ ቅንጂታዊ አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ በማንሳት ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎች መልስ ያገኛል ብሎ ያምናል።

1.መምህራን በክፍል ውስጥ አንብቦ መረዳትንና መጻፍን አቀናጅተው እንዴት ያስተምራሉ ?

2.መምህራን አንብቦ መረዳትና መጻፍን አቀናጅተው ሲያቀርቡ የሚገጥማቸውን ችግር እንዴት ይቀርፋሉ?

3.መምህራን ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅተው ሲያቀርቡ ለተማሪዎች ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

1.3.1 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል መምህራን ትኩረቱን በማድረግ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መተንተን ነው።

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

ከመሰረታዊ ዓላማው በመነሳት የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ቀርበዋል።

1. የአንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ይዘቶች አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ችሎታ በሚያዳብር መልኩ መቅረብ አለመቅረባቸውን መመርመር፣

2 የአንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን የሚመለከቱ የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመር፣

3. አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን መምህራን በክፍል ውስጥ ያቀረቡባቸውን ስልቶች መፈተሽ፣

4. መምህራን ስለማንበብና መፃፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ክንውን ታስቦበትና ታቅዶበት ስለመሆኑ ያላቸውን ግንዘቤ ለይቶ ማውጣት ናቸው።

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ መተንተን መሆኑ በቀደሙት ክፍሎች ቀርቧል። ጥናቱ ሲጠናቀቅ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል ።

በመጽሀፉ የቀረቡት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና የመልመጃዎቹ አቀራረብ እንደት መሆን እንዳለበት የሚተነትን ስለሆነ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ ትኩረት እንዲሰጡት የሚያደርግ ጠቀሜታ አለው።

ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ በሚመለከት መረጃ የሚሰጥ በመሆን ያገለግላል።

ወደ ፊት በዚህና ተያያዥ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናታቸውን ለሚያከናውኑ ሰዎች እንደግብዓት በመሆን ያገለግላቸዋል።

1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህጥናት ትኩረት በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ በጢያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ላይ ብቻ ነው።ስለሆነም ከአንብቦ መረዳትና መጻፍ ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ውጭ ያሉ ጉዳዮችን አያካትትም።

1.6 የጥናቱ ውስንነት

የህ ጥናት የቋንቋ ክሂሎች ማለትም አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ላይ ስለሚያተኩር ውስንነት ይስተዋልበታል ። ስለዚህ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር ላይ ትኩረት ተደርጎ ጥናት ቢካሄድ ውስንነቱ የተዋጣለት ይሆናል ።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ስር የቋንቋ ክሂሎችና የይዘት ምንነት፣ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና የማቅረቢያ ዘዴዎች፣ የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት የመጠቀም ፍይዳ፣ የአንብቦ መረዳት ምንነት፣ የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፣ አንብቦ መረዳትን የማስተማር ሂደት፣ የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ፣ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ፣ የጽሀፈት ክሂል ምንነት፣ የጽሀፈት ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር፣ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች እና የቀደምት ስራዎች ቅኝት የሚሉት ጉዳዮች ቀርበውበታል።

2.1 የቋንቋ ክሂሎች ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት በጽሑፍ አማካይነት የተላለፈ መልእክትን በንባብ አማካኝነት የመቀበል ዘዴ ሲሆን መጻፍ ማለት ደግሞ በጽሑፍ አማካኝነት ለአንባቢ መልእክቱን የማስተላለፍ ስልት ነው።

የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎችንና የይዘት ምንነትን በተመለከተ Widdowson (1978,57) ማንበብና መጻፍ በሚታዩ ምልክቶች አማካኝነት መረጃን መቀበያና ማስተላለፊያ ክሂሎች እንዲሆኑ ማዳመጥና መናገር ደግሞ መረጃንወይም መልእክትን በቃል አማካኝነት ማስተላለፊያና መቀበያ ክሂሎች እንደሆኑ ገልጸዋል።በየትኛውም ሁኔታ የሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት አቢይ አላማ ተማሪዎች ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች በማዳበር በተግባቦት በጥሩ ሁኔታ መገልገል እንድችሉ ማብቃት ነው። በተጨማሪ ተማሪዎች የስነልሳንና የስነጽሁፍ ክሂላቸውን እንድያዳብሩ ይረዳቸዋል።

ከላይ ከቀረበው የምሁራኑ ሃሳብ የምንገነዘበው የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎች መልዕክት የመቀበያና የማስተላለፊያ መሆናቸውን እና እነዚህ መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች የስነ- ጽሁፍና የስነ ልሳን እውቀት እንደሚያጎናፅፉ የሚረዳ መሆኑን ነው።

2.2 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅት ምንነት

ቋንቋ በማስተማር ደረጃ ልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም አይረሴ ተግባር ነዉ።ከእነዚህ ውሰጥ የመማር ማስተማር ግብ እንድሳካ የቋንቋ ክሂሎችን በማቀናጀት ማስተማር አንዱ ዘዴ እንደሆነ Littile Wood,(1981, 93) ገልፀዋል።

አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እያቀናጁ ማስተማር ራሱን የቻለ አንዱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን በተመለከተ Gilbert.J (1982) እውነተኛውን የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴ ስንመለከት ጽሀፈት በንባብ ንግግር በማዳመጥ ይታገዛል።በመማሪያ ክፍል ውሰጥ የሚተገበረው የቋንቋ ትምህርት ዓላማም ተማሪው የቋንቋውን አጠቃቀም በሚገባ እንድገለገልበት ማድረግ ስለሆነ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ መገልገል የተግባቦት ሚናን ለማሻሻል ትልቅ ድርሻ እንዳለው ያብራራሉ።

በተመሳሳይ Byrne(1981, 108) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ሲባል እንዲሁ የሚካሄደውን የቅንጅት ሂደት የሚመለከት ሳይሆን ታስቦበት ተማሪዎች መብቃት እንድችሉና በቋንቋው ተግባቦታዊ እርካታን እንድጎናጸፉ የሚያደርግ ነው።ይኸውም ከትምህርቱ እቅድ ጋር በሚመጣጠን ሁኔታ ትኩረት የሚያስፈልገውን የክሂል ዓይነት በሚገባ ትኩረት እንድሰጠው ለማድረግ ይረዳል።በተጨማም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተሳስረው አንዱ ሲታሰብ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት አብራርተዋል።

ከቀረቡት የምሁራን ሃሳብ መገንዘብ የሚቻለው የቋንቋ ክሂሎችን አቀራረብ ሂደት ስናስብ በክፍል ውስጥ አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታለም የመጻፍ ክሂል አብሮ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ነው።

የመጻፍ ክሂል በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች በተጓዳኝ የሌሎች ክሂሎችን እውቀት ማጎልበት ይችላሉ።ለምሳሌ፡-ድርሰት እንድጽፉ ቢታዘዙ በሚጽፉበት ጊዜ የንባብ ክሂላቸውን ጎን ለጎን ማዳበር ይችላሉ። በቂ የሆነ የማዳመጥ የመናገር ብቃት ካላቸው ደግሞ ጥሩ የሆነ የመጻፍ ክሂል እንደሚያዳብሩ ይታመናል።ስለሆነም አንድን ክሂል ስናስተምር ሌሎችን ክሂሎች እንደምናስተምር እንዲሁም የመጽሐፍ አዘጋጆች መጽሀፍትን ሲያዘጋጁ እነዚህን ታሳቢ ማድረግ እንዳለባቸው Rivers (1981,297) ያብራራሉ።

2.3. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ ዘዴዎች

የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልፃሉ።Celce-Murcua (1991, 313) እና Oxford (2001,3) የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን በማቀናጀት ለማስተማር መምህራን፣የመጽሐፍት፣የመርሃ ትምህርትና የስርዓተ ትምህርት ትኩረት ሠጥተው መስራት እንደሚገባቸው ይገልጻሉ። እንዲሁም ይዘት ላይ ያተኮረ፣ሁሉንም ዘዴዎች ያካተተ፣በተግባር ላይ የተመረኮዘ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በቅንጅት ማቅረብ እንደሚገባቸው ያብራራሉ ።

ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ሃሳብ የሚያስጨብጠው የቋንቋ ትምህርት ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ የመርሃ ትምህርት፣ የመማሪያ መጽሃፍት አዘጋጆች እና አስተማሪዎች ይዘትና ተግባር ተኮር ዘዴ በመጠቀም ማስተማር እንዳለባቸው ነው።

በተጨማሪም Celce-muricia (1991, 316) ይዘት ተኮር የክሂሎች በቅንጅት ማቅረቢያ ዘዴ ዋና ትኩረት ይዘት ላይ ነው።በዚህ ዘዴ ተማሪዎች ይዘቱን ከመማር በተጨማሪ የቋንቋ ችሎታቸውን ከፍ ያደርጋሉ።አያይዘውም ይዘት ተኮር የማቅረቢያ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ይዘት ላይ በማተኮር ጭብጡን እንድረዱት የሚያደርግ አቀራረብ እንደሆነ ሲገልጹ Atkins (1996,223) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዓቢይ ዓላማ ልዩ ልዩ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው በመጠቀም ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ከማዳበሩም በላይ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን በሚገባ እንድገነዘቡ እንደሚረዳቸውም ይገልፃሉ።

ተግባር ተኮር የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ደግሞ ተማሪዎች ተግባር ላይ ባተኮረ የተግባቦት ስርዓት እየሰሩ ቋንቋውን ለመማር ጥረት የሚያደርጉበት እንደሆነናOxford (2001) ይገልጻል።

ከነዚህ ሀሳቦች የምንገነዘበው ይዘት ተኮር የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ የአቀራረብ ዘዴ ትኩረቱ ቋንቋን ከይዘት አኳያ ማስተማር ስለሆነ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂላቸውን እንድያዳብሩ ከማድረጉ በተጨማሪ ልዩ ልዩ ይዘቶችን በሚገባ እንድገነዘቡ የሚያግዝ እንደሆነ ሲሆን በተግባር ተኮር ዘዴ ማስተማር ደግሞ ተግባቦታዊ ሂደትን መሠረት በማድረግ ለማስተማር የሚያገለግል መሆኑን ነው።

2.4.የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ ጠቀሜታ ፡

በቀድምው የቋንቋ ትምህርት ዘመን የቋንቋ ክሒሎችን ለየብቻ በማቅረብ ማስተማር የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ወደኋላ ከመጎተት ባለፈ በሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድር

እንደነበር በማብራራት ለዚህም ምክንያቶቹ ደግሞ የስርአተ ትምህርትና መርሐ ትምህርት ቀራጮች የቋንቋ ክሒሎችን በተናጠል ለማስተማር የሚያስችል አድርገው ማቅረባቸው ነው።በዚህ ሁኔታ የሚማሩ ተማሪዎች የሚኖራቸው የቋንቋ እውቀት ስለቋንቋው ከማወቅ አልፎ በታላሚው ቋንቋ የመገልገልና የመጠቀም ተግባቦታዊ ችሎታቸው በጣም ዝቅተኛ እንደሚሆን Oxford(2001,2) ይገልጻል።

ከሃሳቡ መገንዘብ የተቻለው የቋንቋ ትምህርት ክሂሎች በተናጠል ሲቀርቡ ተግባቦትን የመገደብና ተማሪዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል። ምክንያቱ ደግሞ ቅርፅ ላይ የሚመሰረት በመሆኑ ነው።

በተጨማሪም McDonough and shaw (1992,217) የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመቀስቀስ፣የተማሪዎችን የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ ለማሻሻልና የመማር ማስተማር ተግባርን ለማፋጠን እንደሚጠቅም ያብራራሉ።

ከሃሳቡ መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ክሂሎችን በማቀናጀት ማቅረብ ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የማድረግ ጠቀሜታ ያለው ነው። ተነሳሽነትና ፅኑ ፍላጎት የሚኖራቸው ከሆነ ደግሞ አራቱንም ክሂሎች መገልገል እንዲችሉ የሚያስችል መሆኑን ያስገነዝባል።

2.5 የአንብቦ መረዳት ምንነት

ብዙውን ጊዜ ሰዎች አንብቦ መረዳት አንድን ምንባብ አንብቦ ጥያቄዎችን መመለስ እንደሆነ ያስባሉ። ነገርግን አንብቦ መረዳት ማለት ከጽሑፍ ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ ለይቶ በማውጣት ሃሳብን የመረዳትና ጽሑፍን የመገንዘብ ዘዴ እንደሆነና አንብቦ መረዳት አንባቢዎች ከምንባብ አስፈላጊ መረጃን በመለየት ጥልቅ ግንዛቤ መውሰድን እንደሚመለከት Williams (1990,3) ያብራራሉ።

ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የተቻለው አንብቦ መረዳት ማለት አንብቦ ምላሽ መስጠት ብቻ ሳይሆን መልዕክቱን የመረዳትና ተፈላጊውን ጭብጥ የመቅሰም ሂደት እንደሆነ ነው።

አንብቦ መረዳት ማለት አንባቢው ከሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ እንደየ አስፈላጊነቱ አስፈላጊውን መረጃ መለየት መቻል ነው። አንድ አንባቢ አንብቦ ተረዳ የሚባለው የሚያነብበትን አላማ በመረዳት የተፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት ማውጣት ከቻለ ነው። ስለሆነም አንብቦ መረዳት ማለት አስፈላጊውን መረጃ ከሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ በመለየት ማውጣትና የዚያን ጽሑፍ ጭብጥ የመገንዘብ ሒደት እንደሆነ እንዲሁም የበርካታ ክሒሎች ቅንጅት ውጤት እንደሆነ Grellet(1981,3) ያብራራሉ።

የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስረዳው ተማሪው አቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ ከፅሁፉ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ማውጣት ከቻለ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ያዳበረ መሆኑን ያሳያል።

አንብቦ መረዳት የሚነበብን ጉዳይ ጭብጥ የመረዳት ፣የመተርጎም፣ መገምገም ፣ጽንሰ ሀሳቦችን የመገንዘብ፣ የመከለስ፣ልዩነትና አንድነትን የመመርመር ፣ መወያየት የመከራከር ሀሳቦችን መግለጫ ስለሆነ ከሌሎቹ ሦስት ክሂሎች ተለይቶ አይታይም ።

ጠቅለል ባለ መንገድ "አንብቦ መረዳት አንባቢ የፀሀፊውን ሃሳብና አመለካከት ለመረዳት ሲል ከጽሁፍ ያገኘውን ሃሳብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር እያገናዘበ የራሱን አዲስ አመለካከት የሚንጸባረቅበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል" ሲሉ Durkin (1977, 399) እና Grellet (1991, 8) ገልጸዋል።

የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስረዳው አንብቦ መረዳት የመገንዘብ፣ የመረዳት፣ ሃሳብ የመለዋወጥ፣ የመደጋገብ፣ የማረምና የመመርመር ስራዎችን የሚጠይቅ መሆኑን ነው።

2.5 .1 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

ንባብ በማንኛውም መቼት ጽሑፋዊ የመረጃ ማቀበያ ከሆነው የጽሀፈት ክሂል ሀሳብን የምናካብትበት ቀዳሚው ክሂል እንደሆነ ይታወቃል።Williams (1990,19)የንባብን አስፈላጊነት ሲገልጹ"አንድን የተጻፈ ነገር አንብቦ ሀሳቡን የመገንዘብ ችሎታን ለማሳደግ፣በንባብ አማካኝነት እውቀትን ለማካበት እንድሁም ከልዩ ልዩ የንባብ ደረጃዎች ጋር ለማገናኘትና የንባብ ችሎታን ለማዳበር ያገለግላል "ይላሉ።

"ንባብ መረጃ ለማግኘት፣ አንድ ነገር መቼና የት እንደተከናወነ ለማወቅ እንዲሁም በጋዜጦችና በመጽሄቶች የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ይህ ክሂል እንዲዳብር የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን" ሲሉ Mc Donough and Shaw (1993, 102) አብራርተዋል።

ጠቅለል ብለው የቀረቡት የምሁራን ሃሳቦች የሚያስረዱት የማንበብ ክሂል ትምህርት አንብቦ መልዕክትን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣ በማንበብ እውቀትን ለመቅሰም፣ አንድ ታሪክ የተከናወነበትም ጊዜና ቦታ ለማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ነው።

የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማጎልበት የሚዘጋጁ ጽሑፎች የሚከተሉትን ነገሮች ታሳቢ ማድረግ ይገባቸዋል።እነዚህም፡-

ርዕሰ ጉዳይ፡- ለንባብ የተመረጠው ጽሑፉ የተማሪዎችን ዳራና ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት ።

ደረጃ፡-የሚመርጠው ጽሑፍ የተማሪዎችን እውቀትና ደረጃ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል።በጽሑፉ ውስጥ የተካተቱት ቃሎች፣ዓረፍተ ነገሮች መወሳሰብ ከተማሪዎች የእውቀት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ ሊሆን ይገባዋል።

የጽሑፍ ብዛት (መጠን)፡- የሚመረጠው ጽሑፍ ርዝመትና ስፋት ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ አኳያ የተመጠነ መሆን አለበት። ምክንያቱም "አንድን የተጻፈ ነገር ለማንበብ የምንጠቀምበት ጊዜ እና ከንባብ በኋላ ለምናከናውነው ተግባር የሚኖረን ጊዜ ከአጠቃላዩ ሰዓት ጋር የተመጣጠነ ካልሆነ ልናጎለብተው ያሰብነውን የአንብቦ መረዳት ክሂል በሚገባ ውጤታማ ልናደርገው አንችልም"ሲሉ ክንያቱም "በማለት Lindsay and Knight (2006, 74) አቅርበዋል።

2.5.2 አንብቦ መረዳትን የማስተማር ደረጃዎች

አራቱም የቋንቋ ክሒሎች ትምህርት የታሰበውን ዓላማ እንድያሳኩ በዚህ መስክ ጥናት ያካሄዱት ምሁራን ጥሩ የሚሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች ያቀርባሉ።ሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ትምህርት የታለመላቸዉን ግብ እንዲመቱ በመስኩ ጥናት ያደረጉ መምህራን የተሻለ ነዉ የሚሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች እና ሂደቶች ያቀርባሉ።ከእነዚህም ጌታቸው(1996)፣አዜብ (1984)ን በመጥቀስ “የአንድ መምህር ዉጤታማ የማስተማር ተግባር መገለጫዎች መካከል የቀረበለትን መሰረታዊ የማስተማሪያ ዘዴ እና ሂደት ተከትሎ በክፍል ዉስጥ ማስተማር ነዉ" ሲሉ አብራርተዋል። ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ክሔልን በክፍል ውስጥ ስመጠቀም ልንከተላቸው የሚገቡ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የቅድመ ንባብ ተግባራት፡- የቅድመ-ንባብ ተግባራት ሂደት ዓቢይ ዓላማዎች አሉት።እነዚህም ተማሪዎቹ ምንባቡን ለምን ዓላማ እንደሚያነቡት በማስገንዘብ ፍላጎታቸውን መቀስቀስና ማነሳሳት ስለ ምንባቡ ፍንጭ እንድኖራቸው ማድረግ እንደሆነ ጌታቸዉ(1996) ይገልጻሉ።በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ምን ያህል ትኩረት ሰጥተው ማንበብ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ።።በዚህ የአቀራረብ ስልት "ተማሪዎች ጽሁፍን ወደማንበብ ተግባር ከመሸጋገራቸዉ በፊት ከእርእሱ ጋር በተያያዘ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነሳሳት በምንባቡ ዉስጥ የሚገኙ ለንባብ እንቅፋት ይሆናሉ ተብለዉ የሚገመቱ ቃላትን ወይም ሐረጋትን ፍቸዎች እንዲረዱ የማድረግ ተግባራትን ያካትታል" በማለት Nuttal(1982) ገልፀውታል።

"ተማሪዎችም ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከቀድሞ ዕዉቀታቸው በመነሳት አንዳንድ ሀሳቦችን በመሰንዘር ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ፍጹም ሆኖ አይታያቸዉም "Stateman(1981)።በሌላ መንገድ

"ተማሪዎች ምን እንደሚያነቡ ለቀጣይ ደረጃ (የንባብ ጊዜ) ተግባራትን ማስተዋወቂያ ነዉ" በማለት McDonugh and Shaw(2003) ገልጸውታል። በአጠቃላይ በዚህ የቅድመ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች ፡-

ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ የግንዛቤ መገምገሚያ ጥያቄዎችን የቅድመ ንባብ እውቀታቸውን በመጠቀም እየመለሱ ይነቃቃሉ ።

ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡት በመረዳት የንባብ ፍላጎታቸው እንዲቀሰቀስ ይደረጋል።

ስለምንባቡ ይዘት እንዲረዱና እንድገምቱ ይደረጋል። በጠቅላላው የቅድመ ንባብ ተግባራት ዓቢይ ዓላማ ተማሪዎች የሚያነቡትን ምንባብ በሚገባ እንድረዱትና የንባብ ፍላጎታቸው እንዲዳብር ይጠቅማቸዋል።

የንባብ ጊዜ ተግባራት፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ የሚያነቡበት ነው።ስለዚህ ተማሪዎች ጽሑፉን አንብበው በትኩረት በመረዳት ሃሳብ እንድሰጡ መምህራን ያነሳሳሉ ፣Wallas(1992)። ብዙ ጊዜ ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍ ተማሪዎች በእርጋታ እንድያነቡት ይደረጋል። በጥቅሉ በንባብ ጊዜ መምህራን ክፍሉን የመምራትና የመቆጣጠር ተግባራትን እያከናወኑ Greenwood (1981)፣ Nattual (1982) እንደሚገልጹት ተማሪዎች፡-

የምንባቡን ዓላማና ይዘት እንድገነዘቡት ማድረግ ፣

በምንባቡ ውስጥ ልዩ ልዩ የንባብ ዘዴዎችን እንድጠቀሙ ማድረግ፣

የንባብ ጊዜ ሰዓታትን ከግምት ውስጥ ማስገባት የመሳሰሉትን ተግባራት ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በንባብ ጊዜ ተግባራት ተማሪዎች፡-

በየምንባቡ መካከል ዋና ዋና ሀሳቦችን መለየት፣

የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች በወረቀት ላይ ማስፈርና

ከንባቡ በመጨረሻም በሚገባ ያልተገነዘቡት ነጥብ ካለ እንደገና አንድ በአንድ እንድመረምሩት ማድረግ አለባቸው።

የድኅረ ንባብ ተግባራት ፡- ይህን የንባብ ደረጃ ለትምህርቱ የሚቀርበው ምንባብ በቋንቋ ትምህርቱን ውስጥ ጉልህ ትርጉም እንድኖረው የሚደረግበት ደረጃ እንደሆነ Greenwood(1981) ያብራራሉ። ይህ የንባብ ደረጃ ተማሪዎቹ ያነበቡትን ነገር በሚገባ እንድገነዘቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በመስጠት መልስ እንድያቀርቡና እንድወያዩ የሚደረግበት ነው።የእነዚህ ጥያቄዎች ዋና ዓላማም የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ብቃት ማጎልበት እንደሆነ Greenwood(1981) ተናግረዋል።በሌላ መልኩ Lindsay(2006) እንደገለፁት መምህራን በድህረ ንባብ ደረጃ ፡-

የጽሑፉን ጭብጥ መገንዘብ መቻላቸውን ለመረዳት ለተማሪዎች ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣

ጽሑፉን እንድገመግሙ ማነሳሳት፣

የጽሑፉን ጭብጥ ከራሳቸው ህይወት ጋር በማዛመድ ተማሪዎች ንግግር እንድያዘጋጁ ማድረግ ወዘተ.ይገባቸዋል።

በድኅረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በቡድን በመደራጀት በጽሑፉ ላይ በትኩረት በመወያየት የተለያዩ ጥያቄዎችንና ዋና ዋና ሀሳቦችን የሚለዩበት ነው። ይህም "እያንዳንዱ ተማሪ የመለሰዉን መልስ ለምን እንደመረጠዉ የማስረዳት ዕድል ይሰጣል። በዚህም ዕድል መኖር አንድን ምንባብ አንብበዉ ምን ያህል እንደተረዱት ጥያቄዎቹ በሚሰሩበት ወቅት የትና እንዴት እንደተሳሳቱ ሊያዉቁ ይችላሉ" ብለዋል Nuttal (200)::

የአንብቦ መረዳት ክሒልን በክፍል ውስጥ ስናስተምር የምናከናውናቸው ተግባራት አሉ። እነዚህም ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ወቅት(ጊዜ) እና ድህረ ንብ ተግባራት ናቸው። በእያንዳንዳቸው ስር ተግባሮችን በማከናወን የክህሎት ትምህርቱን ለተማሪዎች ማቅረብ ተገቢነት አለው። እነዚህም አንብቦ መረዳትን ማስተማር የተግባር ሂደቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው።

2.5.3 የማንበብ ክሂልን የማስተማር ዓላማ

እንደ Williams (1993) የንባብ ክሂልን የማስተማር ዓላማዎች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የድምጾችን የንባብ ሁኔታ ፣ መጥበቅና መላላት፣ ፊደላትን መለየት፣የተለያዩ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን ከፍ ባለ ድምጽ በማንበብ ነው።የዚህ አይነት ንባብ አስፈላጊ የሚሆነው ለጀማሪ አንባቢያን ብቻ ነው።ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ፊደላትና ድምጾች በጥሩ ሁኔታ ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ፣ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የቋንቋውን ድምጾች፣የፊደላትና ቃላት ከንባቡ ለመረዳት ሊረዳቸው ይችላል ።

በጠቅላላ የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስረዳው የማንበብን ክሂል የማስተማር ዓላማ ከድምፆች ንበት ጀምሮ ዓረፍተ ነገሮችን በሚገባ ማንበብ የመቻልን ደረጃ እንደሚያልፉ ነው።

2.6 የመጻፍ ክሂል ምንነት

የመጻፍ ክሂል የንግግር ድምጾችን በምልክት አማካኝነት መልእክትን በጽሑፍ በማስቀመጥ የመግባባት ዘዴ ነው።

እንደ Byrne(1988) ገለፃ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገልጹ የንግግር ድምጾች የየራሳቸው ምልክታዊ ውክልና ይኖራቸዋል።ምልክቶቹ የቋንቋውን ስርዓት ተከትለው ይደራጃሉ።ታዲያ እነዚህ ድምጾች በዚህ መንገድ ተዋህደው ትርጉም እንድኖራቸው የሚደረጉበት ሂደት ጽህፈት ይባላል።

ጽህፈት ድምፅን አቀናጅቶ ቃላት ከመመስረት ጀምሮ ዓረፍተ ነገሮችን የማዋቀርና አንቀፆችን የመፃፍ ሂደትን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑን ያስረዳል።

በሌላ ገለፃ Harmer(1991፣149):(Nunnan(1988:36) እና Byrne(1991) "አንድን ጽሑፉ በምናዘጋጅበት ጊዜ የተለያዩ ትዕምርቶችን እንጠቀማለን።እነዚህ ትዕምርቶች የሚመሰርቷቸው ፊደላትና የፊደላት ግንኙነት ሲሆን ከድምፅ ጋር ይገናኛሉ።ነገር ግን ንግግር ከድምፅ በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም በዓይን የሚታዩ ትዕምርቶችን ከማፍለቅ በላይ ነው"ይላሉ።

ከምሁራን ሃሳብ መረዳት የተቻለው ጽሁፍ ለመፃፍ ምልክቶችን የምንጠቀም መሆኑን ነው። ምክንያቱም ምልክቶች ፊደሎችንና የፊደሎችን ግንኙነት ይፈጥራሉ።

Byrne (1988) በበኩላቸው በሚፃፍበት ወቅትም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምና ሥርዓት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ጽህፈት እንደ ቃላዊ ክሂሎች በመልመድ ሳይሆን በመማር የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ትጋትንና ጥረትን የሚጠይቅ የቋንቋ መሠረታዊ ክሂል ነው። መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው። ስለዚህ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን የመጻፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለጻል። መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያቶች ስነልቦናዊ ችግር፣ ሰዋሰዋዊ ችግርና ግንዛቤዊ ችግር ናቸው ይላሉ።

በሚፃፍበት ጊዜ ከቃላት አጠቃቀም ጀምሮ፣ የሃሳብ ፍሰት፣ አወቃቀር፣ የአገላለፅ ብቃትና ስልት ሌሎችንም ጨምሮ መገንዘብ ወይም በደንብ ማጤን እንደሚገባ የሚያስረዳ

ነው።

2.6.1 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

ጽህፈት ሲዘጋጅ ከአንባቢ ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል። Raimes (1983፡ 3) "ሰዎች በጊዜና በቦታ ሳይገደቡ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካኝነት ከማግባባቱም በላይ ለትምህርት መማሪያ፣ ለሀሳብ መለዋወጫና ለመሳሰሉት ነገሮች እንደሚያገለግል ይገልፃሉ። ይህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቱ ደግሞ በትምህርትነት እንዲሰጥና እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል"ብለዋል።

ምሁራኑ የሚያስረዱት የጽሀፈት ትምህርት አስፈላጊነት መካከል ለሃሳብ መለዋወጫነት በመሆንም የሚያገለግል እንደሆነ ነው።

እንዲሁም Celece Murcia (1991፡ 241) በበኩላቸው "ተማሪው በተሻለ ሁኔታ በቋንቋው እንዲጠቀምና የተግባቦቱን ሂደትም በጥልቀት እንዲመረምር ያደርገዋል" ይላሉ።

ከምሁራን ሃሳብ መገንዘብ የሚቻለው የጽሀፈት ክሂል አስፈላጊ የሚሆነው የእርስ በርስ ተግባቦትን ጥልቅ በሆነ መልኩ ለመመመርመር የሚያስችል እንደሆነ ነው።

በተመሳሳይ Ur (1996፡ 168) የጽሀፈትን ትምህርት ከግለሰብዓዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ይመለከቱታል። ግለሰባዊ ፋይዳው አመለካከትን ከመግለፅ፣ የተፃፉ ሰነዶችን ከመመርመርና አዕምሯዊ ተግባራትን ከመመርመር አንፃር ሲተነትኑት ማህበራዊ ፋይዳውን ደግሞ የማህበረሰቡ የሆኑ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ባህላዊ መገለጫዎችን፣ ሥነጽሁፋዊ ስራዎችንና የመሳሰሉትን ለመሰነድ ካለው ፋይዳ አንፃር ገልጸውታል።

2.6.2 የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች

የፅህፈትን ክሂል ለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ የአቀራረብ ዘዴዎች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ ግን ተቀባይነትን አግኝተው በስፋት እየተሰራባቸው ያሉት ውጤታዊ አቀራረብ (product Approach) እና ሂደታዊ አቀራረብ (process approach) ናቸው በማለት Raimes, (1983), Brown, (1994), Richards, (1990), Leki, (1996), Silva (1990) ከፋፍለው አቅርበውታል::

"ውጤታዊ አቀራረብ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ፅህፈትን (ድርሰትን) በማስተማር ሂደት ሲያገለግል የኖረና በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ያለ ነው። ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሚፅፉት ድርሰት የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርፅ ላይ ነው" በማለት (Richards, 1990) ገልፀዋል።

ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናል ወይም ጥሩ ተፅፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀቶችን፣ የአፃፃፍ ብልሃትን፣ ወዘተ. በማሳየት ተማሪዎች እነዚያን አስመስለው እንዲፅፉ የሚያለማምድ ነው ሲሉ Nunan (1989, 36) እና Richards (1990, 106) አቅርበዋል።

የምሁሩ ሃሳብ በሞዴልነት አንድ ጽሁፍ ካቀረቡላቸው በኋላ ሞዴል ጽሁፉን አስመስለው እንዲጽፉ በማድረግ ማለማመድ እንደሚገባ ያስረዳል።

በውጤታማ አቀራረብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው የፅሀፈት ተግባራት በቋንቋው ሰዋሰው ላይ ያተኮሩ ናቸው። ተማሪዎች በሞዴልነት በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ፆታን፣ ጊዜን፣ ቁጥርን፣ ወ.ዘ.ተ በመቀያየር የሚለማመዱባቸው ጠቋሚ መልመጃዎች ይቀርባሉ። በመምህሩ ተመርጦ በሚሰጣቸው ርዕስ ድርሰት ሲፅፉ መጀመሪያ ትኩረታቸውን በቋንቋው መዋቅር ላይ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ሰዋሰዋዊ ስህተቶቻቸውንም ለማስወገድ ሲሉ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያደረጋል Leki, (1996

ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚገኙ ተማሪዎች የዚህ አቀራረብ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀፆችና አውድች መዋቅርና አደረጃጀት ላይ ነው። ዓላማውም ትክክለኛ ፅሁፎችን (ድርሰቶችን) ማፍለቅ ነው። ዋና ዋና ባህሪያቱና መርሆዎቹ የሚከተሉት መሆናቸውን Richards (1990, 30-32) ይገልፃሉ።

የፅሀፈት ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸው የቋንቋ ቅርፅና አደረጃጀት ላይ ያተኩራል። ትክክለኛ የዓረፍተ ነገር መዋቅር መስራት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው። ስለዚህም የሰዋሰው ችሎታ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲፅፉና ስህተት እንዳይፈጽሙ ለማድረግ ይሞከራል። የእጅ ፅሁፍ፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል ወ.ዘ.ተ እውቀቶች በትምህርት ይሰጣሉ። የፅሀፈት ደረጃ በውጤታዊ አቀራረብ ፅሀፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ። እነዚህም ተግባራት ውስን ፅሀፈት፣ መር ፅሀፈትና ነፃ ፅሀፈት ደረጃዎች ናቸው በማለት (Pincas, 1982፣ 14)፣ Raimes, (1983 ፣7) Richards እና (1990፣ 107) ያቀርባሉ።

የምሁሩ ሃሳብ የሚያስጨብጠው ጉዳይ ጽህፈት ዓላማ የሚያደርገው የቋንቋ ቅርጽና አደረጃጀት ላይ በማተኮር ከእጅ ጽሑፍ ጀምሮ እውቀቶችን አስጨባጭ መሆኑን መረዳት ላይ ነው ።

ሀ) ውስን ፅህፈት (Controlled Writing) ለመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች የፅህፈት ትምህርት የሚቀርብና የውስንነት ደረጃው ፍፁም ወይም አንፃራዊ የሆነ ክንውን ነው። የዚህ የፅህፈት ስራ ዋና ዓላማ ተማሪዎች አንፃራዊ በሆነ መንገድ ከስህተት የፀዳ ፅሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ነው። በውስን የፅህፈት ደረጃ ፅህፈትን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ውስን የሆነ ማሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸው። በውስን ፅህፈት ደረጃ ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣ በሠንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዓረፍተ ነገር መመስረት፣ ቅደም ተከተላቸው የተፋለሰ ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ ነገር መስራት፣ በአንቀጽ

ውስጥ የቁጥር፣ የፆታ ፣ የጊዜ እና የመደብ ለውጥ በማድረግ እንደገና ለመፃፍ ያስችላል በማለት (Doff, 1988) ገልፀዋል።

ውስን ጽሀፈት ባዶ ቦታዎችን የመሙላት፣ ሰንጠረዦችን ወደ ዓረፍተ ነገር መለወጥ፣ ዓረፍተ ነገሮችን በሃሳብ ቅደም ተከተላቸው አስተካክሎ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ማስገኘት፣ በመደብና በፆታ አስተካክሎ ማሳየት እንዲችሉ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል።

ለ) መር ፅሀፈት (Guided Writing) መር ፅሀፈት በውስንና በልቅ ፅሀፈት መካከል እንደ መሸጋገሪያነት ሆኖ የሚያገለግል ነው። ይኸውም ተማሪዎች በውሱን ፅሀፈት ደረጃ ካዳበሩት መሰረታዊ የዓረፍተ ነገር የአፃፃፍ ብቃት በተጨማሪ የአፃፃፍ ስሌት ለመለየት የሚያግዙና ወደ ነፃ ጽህፈት (Free Writing) የሚያሸጋግሩ ይዘቶችን የሚይዝ በመሆኑ ነው። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህራን በሚያቀርቡላቸው ሞዴል መሰረት የፅሀፈት ልምድ እንዲኖራቸው ያደርጋል በማለት Doff (1988, 62) Raimes (1983, 103) እና Pincas (1982, 102) ይገልፃሉ።

የቀረበው ሃሳብ የሚያስገነዝበው አስተማሪው ለተማሪው ሞዴል ጽሁፍ ካቀረበላቸው በኋላ ልምምድ እንዲያደርጉ እድል የሚሰጡበት መር ጽህፈት እንደሚባል መረዳት ተችሏል።

ሐ) ነፃ ወይም ልቅ (Free Writing) በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛው መምህራን በሚሰጧቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ አፍልቀው በራሳቸው ቋንቋና አገላለፅ ድርሰት የሚጽፉበት ነው (Pincas, (1982) እና Raimes, (1983) ብለዋል::

ስለነፃ ጽህፈት የቀረበው የምሁራን ሃሳብ የሚያስረዳው ተማሪዎች በራሳቸው ወይም እንዲጽፉበት በሚሰጣቸው ርዕስ ዙሪያ በራሳቸው የቋንቋ አጠቃቀም ብቃትና የሃሳብን የመግለጽ ችሎታ የሚለማመዱበት የማስተማር ሂደት መሆኑን ነው።

ድርሰት የመፃፍ ስራ የሚጀምረው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ቅርፆች ከመለማመድ ነው። ከልምምድ ቀጥሎ ለሚጽፉት የድርሰት ዓይነት ሞዴል ይቀርባል። ነፃ ፅሀፈት ለሰዋስዋዊ አጠቃቀም እና ለስርዓተ አፃፃፍ ትኩረት የሚሰጥ፣ እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የሚገልፁበት እድል ይሰጣል።" ነፃ ፅሀፈት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚፅፉበት ደረጃ ቢሆንም የፅሁፋቸው መለኪያ ምን፣ እንዴት፣ ለማንና ለምን ተፃፈ? የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ የሚነሱት ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ጽሑፍ ቀርቧልን?የሚለው ነው። ስለሆነም የተማሪዎቹ ልዩ ትኩረት

የሚያርፈው ሀሳባቸውን በመግለፅ ላይ ሳይሆን በፅሁፋቸው ተገቢነት ወይም ብቃት ላይ ነው "በማለት Byrne(1991,16) እና Pincas(1982) ይገልጻሉ።

የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስረዳው ነፃ ጽህፈት ለስርዓተ ጽህፈትና ለሰዋስዋዊ አጠቃቀም ትኩረት ከመስጠት የሚጀምር መሆኑን መገንዘብ የሚቻልበት ነው።

2.7 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር

በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሒሎች መካከል የጠነከረ ግንኙነት ያለ በመሆኑ በቅንጅት ወይም በጋራ ቢቀርብ ጥሩ ነው።የመጻፍ ክሒል የአንብቦ መረዳት ክሒልን ሊያዳብር ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሒልን ሊያዳብር ይችላል።ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን የተጻፈ ነገር ሲያነብ የታሪክ አወቃቀሩን፣የአጻጻፍ ስልቱንና የጽሑፉን ጭብጥ በመረዳት በራሳቸው ለሚጽፉት ጽሑፍ ይጠቀሙበታል።ይህም በእነዚህ ክሒሎች መካከል ያለውን ትስስር እንደሚያመለክት Harp.et.al (1996) ይገልፃሉ።

እንዲሁም Ruddel (1997) የጽህፈት እና የማንበብ ክሒሎች የጠነከረ ትስሰር ስላላቸው በቅንጅት ቢቀርቡ የተማሪዎችን የሁለትዮሽ ክሒሎች ግንባታ ያዳብራል።Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ። የሚማሩትን ትምህርት ይዘት በጥሩ ሁኔታ እንድረዱት ያግዛቸዋል።

በተጨማሪም May(1990) ተማሪዎቹ ውስብስብ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን በሚጽፉበት ወቅት የአንብቦ መረዳት ብቃታቸው ሊዳብር ይችላል።990) በተመሳሳይ ተማሪዎቹ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል።ጸሐፊያንና አንባቢያን የሚተገብሯቸው ተግባራት በመስታይት ውስጥ እንደሚታይ ቁስ አካልና ምስሉን ያህል ትስሰር አላቸው። ይኸውም ለመጻፍና ለማንበብ የራሳቸውን አላማ ይነድፋሉ፤ፍላጎታቸውን ይወስናሉ፤የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤አእምሯዊ ትዕምርቶችን ይፈጥራሉ። የደራሲያን አላማ የውስጣቸውን ስሜት ለሌሎች ማካፈልና መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን እንድዝናኑ ማድረግ ሊሆን ይችላል።ስለሆነም የሁለቱም የመግባቢያ መንገዳቸው የሚዘጋጀው በጽሑፍ ነው። የአንባቢያን ፍላጎታቸውን ደግሞ መልእክት መውሰድ፣ሀሳብን መጋራት ወይምመመዝናናት ሊሆን ይችላል።ነገር ግን ሁለቱም በድርሰት አደባባይ ይገናኛሉ።

ሃሳቡ የሚያስረዳው የሚፃፉ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች አንብቦ የመቅሰም ብቃት አጎልባች መሆኑን ነው። ይህም መፃፍ ሲኖር ማንበብ፣ ማንበብ ሲታሰብ ደግሞ መፃፍ አይቀሬ መሆኑን ነው።

2.7.1 የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሒል ቅንጅት አስፈላጊነት

እንደ Grellet (1991, 4-5) ገለጻየተለያዩ የቋንቋ ክሒሎችን ለማዳበር ልዩ ልዩ ጥያቄዎችበማዘጋጀት ማቅረብ ያስፈልጋል። ጥያቄዎቹም ከምንባቡ አጠቀላይ አደረጃጀት እስከ ዝርዝር ይዘቶች ድረስ ሊያተኩሩ ይችላሉ። የጠያቄዎቹ ተግባርና በአይነትም የተወሰነ ክሒልን ከማዳበር ጋር የተያያዘ ሊሆን ይገባዋል። ይህም የንባብ ክሒልን ለማስተማር ለተማሪዎች በሚዘጋጁ ጥያቄዎች ሊረጋገጥ ይችላል። ጥያቄዎችም አንዱን የቋንቋ ክሒል ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የቋንቋ ክሒሎች ሊያዳብሩ ይገባቸዋል።

ሃሳቡ የሚያስረዳው የመፃፍ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጥያቄዎች የማነንበብ ክሂልን ሊያሳድግ የሚችል ስለሆነ በቅንጅት መቅረባቸው አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

ጽሑፍና ንባብ፡- ተማሪዎች የንባብ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ከዚሁ ጋር አብረው ሊያዳብሩት ከሚገባው ክሒል ውስጥ አንዱ የመጻፍ ክሒል ነው።የጽሑፍ ክሒልን በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን አማካኝነት ለማዳበር ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራትን ማቅረብ ይጠበቃል። ለምሳሌ፡-ተማሪዎች ማስታዎሻ እንድይዙ ማድረግ፣ሀሳቦቻቸውን በአጭር በአጭሩ በጽሑፍ በማስቀመጥና አብራርተው በጽሑፍ በማቅረብ የጽሕፈት ክሒላቸውን ከንባብ ጋር በተቀናጀ ዘዴ ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንብቦ መረዳት ከመፃፍ ክሂል ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው።

እንደ Conley (1997) ገለጻ የመጻፍና የማንበብ ተግባራትን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የሁለቱን ክሒሎች ለማዳበር ወሳኝ ዘዴ ነው።

ከላይ ከምሁራኑ እንደምንረዳው ለመጻፍና ለማንበብ ክሒሎች ትኩረት በመስጠት በቅንጅት በመጠቀም በጋራ ማዳበር ይገባል።

2.7.2 የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሒሎችን ለማዳበር የሚረዱ ብልሐቶች

የመጻፍና የማንበብ ክሒሎችን አቀናጅቶ ማስተማር የቋንቋ ክሒሎችን ለማጎልበት ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ዋና ጉዳይ ነው።በተጨማሪም በቋንቋ ትምህርት ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሑፍን ማዋቀርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ብዙ ዘዴዎች አሉ። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ጽሑፎችን አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ካለምንም ግራመጋባት አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ዘዴዎች ውስጥ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣መተርጎምና ማብራራት፣ማጠቃለል፣መተንበይና መገመት እንዲሁም

በጥልቀት ማሰብና ማገናዘብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።እነዚህንም እንደሚከተለው እያንዳንዳቸው እንመለከታለን።

ጥያቄ መጠየቅ፡-ጥያቄ መጠየቅ፡-"ተማሪዎች አዳዲስ ጽንሰሀሳቦችን ቀድሞ ከሚያውቁት ጋር አቀናጅተው እንድያደራጁ ይጠቅማቸዋል።ጥያቄዎችን የመጠየቅ ስራ በራሱ እውቀትን የማዳበር ተግባር ነው"በማለት Block(1997) ሲገልጹ ።Airasian(1997) ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ጥያቄ ካቀረቡ ሀሳባቸውን በቃላት አማካኝነት እንድገልጹ በጥልቀት እንድያነቡና ትምህርቱን ትኩረት አድርገው እንድከታተሉት ስለሚያስችል አስፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው።

መተንበይና መገመት፡- መተንበይና መገመትን በሚመለከት Blocj(1997) "መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለ ቀጥሎ የሚከናወነውን ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቁምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው።። መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኝን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቁምበት ልዩ ስልት ነው"ይላሉ።

መተንበይ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አነድን ጽሑፍ በማንበብ ላይ እንዳሉ የገጸባህርያትን ድርጊት፣ማንነት ፣ሴራ ወዘተ.በመገንዘብ ንባቡን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊሆን ስለሚችለው ድርጊት በመገመት መጨረሻ ላይ ይደርሳሉ።ይህ ደግሞ የሚያሳየው ተማሪዎች ጽሑፉን መገንዘባቸውን በጽሑፍ አማካይነት የሚገልጹበት እንደሆነ አብራርተዋል።እንዲሁም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሒልን በማቀናጀት ለማስተማር ከሚጠቅሙ ዘዴዎች መካከል መተርጎምና ማብራራት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ Block(1997) ያስረዳሉ።

የቀረበው ሀሳብ ብልሀቶች በሚከናኑበት ጊዜ ስላነበቡት ጽሑፍ ዝርዝር ትንታኔ፣ትርጉምና ትንተና በጽሑፍ ማቅረብ የሚችሉበት ሁኔታ የሚመቻችላቸው መሆኑን ያስገነዝባል።

በሌላ በኩል Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው የንባብ ጊዜ በኋላ በሚያዘጋጁት የውይይት ተግባራት ሀሳባቸውን እንድለዋወጡ የሚያነሳሱ መሆን ይገባቸዋል።ከዚህ ተግባር በኋላ ተማሪዎቹ ስለጽሑፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፤ትርጉም ይሰጣሉ ፤ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይፈልጋሉ።እንዲሁም ተማሪዎች ስለጻፉት ወይም ስላነበቡት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው እንደሆነ ያሳያል።ይህ ስልት በቋንቋ መማር ማስተማር ውስጥ የመጻፍና የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ዘዴ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ።

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ከተማሪዎች የጽሀፈት ልምምድ በኋላ የተማሪዎችን ውይይቶችን በማመቻቸት እርስ በርሳችሁ እንድያስተካክሉ፣እንድገምቱ፣የታያቸውን ሃሳብ እንድገልጹ እናእንዲተረጉሙ እንዲሁም መልእክቱን እንዲገነዘቡ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል።

ማጠቃለል(Summerizing)፡- እንደ Blocj and Mangeri(1995) ማብራሪያ ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሑፍ በህሊናቸው የታሰበውን በጽሑፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም ለረጅም ጊዜ በአዕምሮ ይዞ የማቆየት ችሎታቸው ይጨምራል።በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በእለት ከእለት ህይወት ውስጥ ማከናወን ያስችላል። ስለሆነም ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በየደረጃቸው በጽሑፍ ማጠቃለያ እየሰጡ ማለፍ የሚያስችላቸውን ዘበመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችሏቸውን ዘዴዎች መማር ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ለመጻፍ ያሰቡትን ነገር ከጻፉ በኋላ ጠቅለል አድርገው እንደሚያቀርቡት መገንዘብ ተችሏል።

2.8 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

አጥኚው በርዕሱ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሩ በፊት ከርዕሱ ጋር ተዛምዶ (ተቀራራቢነት) ያላቸውን የቀደምት ስራዎች ዳሰሳ አድርጓል። ሆኖም ግን በርካታ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተጠኑ ቢሆንም ሁለቱን ጥናቶች በማንበብ የሚከተለውን ቅኝት በማድረግ ማቅረብ ተችሏል።

ታረቀኝ አይሶ (2013) “የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ” (በሠኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኪሪነት) በሚል ይዘት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ ነው። ዓላማውም የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ክሂልን ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት በማስተማር ለክሂሎቹ መሻሻል ያለዉን ሚና መፈተሽ በሚል የቀረበ ነበር። በጥናቱ የተረጋገጠው ውጤትም በክሂሎቹ ቁርኝታዊ አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መሻሻል ያሳየ ስለመሆኑ ምርምሩ አሳይቷል። ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለዉ ፈተና ነው። መረጃውን ለመተንተኛነት የተጠቀመው ደግሞ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ሲሆን፤ በጥናቱ የተደረሰበት መደምደሚያ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ በማስተማር የተማሪን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ብቃት ማሻሻል እንደቻለ የተገኘው የውጤት ንጽጽር ማየትና ማወቅ የተቻለበት ነው። ስለሆነም እነዚህን ክሂሎች ይበልጥ በማዳበር በትምህርት ቤቱ የስነጽሑፍ፣ የድራማ፣ የሚኒሚዲያ ተወካይ ባለሙያዎች ተማሪውን በነዚህ ክበባት እንዲመዘገቡ ቢያደርጉና የተዘመገቡ አባላትም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከተለያዩ መጽሀፍትና መጽሔቶች አንብበው

የተረዱትን በጽሁፍ አጠናቅረዉ በየጊዜው በሰንደቅ ዓላማ፣ በዕረፍት ጊዜያቸው በንባብ እንዲያቀርቡ ቢያደርጉ፤ የሚል አስተያየቶች አጥኚዉ ሰጥቷል። ከዚህ ጥናት ጋር በመነሻ ርዕሱ ሲመሳሰል የታረቀኝ ጥናት ተማሪዎች ላይ መሰረቱን ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በመምህራን አቀራረብ ላይ መሆኑ አለያይቷቸዋል።

እመቤት እሸቴ (2011) “አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና” (በ7ኛ ክፍልየአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተተኪሪነት) ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን፤ የጥናቱም ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የክፍል ደረጃ ተዘጋጅቶ በ2008 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው "የ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ላይ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጂታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። ከጥናቱ ዓላማ የተገኘው ውጤትም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶች አቀራረብ ለመማር ማስተማር ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ ልምምድ አመቺ መሆናቸውን፤ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ያስገቡ መሆናቸውን፤ የመማሪያ መጻህፉ አቀራረብ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ እንድዘጋጁና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር እገዛ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በአንጻሩ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን የሚመለከቱ መልመጃዎች አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ስዓት ጋር ያለመጣጣም ችግሮች መኖራቸውን፣ አልፎ አልፎ ስለ መልመጃዎች አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጻሃፉ ውስጥ መካተታቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በመሆኑም የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ላይና በመምህራን ቅንጂታዊ አተገባበር ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ስልቶች በመፍትሔ ሃሳቦች ስር ተጠቁመዋል። ከአሁኑ ጥናት ጋር በመነሻ ርዕሳቸው ሲመሳሰል የጥናቱ ቦታና ዘመን እንዲሁም ተጠኝዎቹ እንዲለያዩ አድርጓቸዋል።

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ

3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ በጢያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል መምህራን አንብቦ የመረዳትና መፃፍ ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ላይ የሚያተኩር ሲሆንየጥናቱ የመረጃ ምንጮች በጢያ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። መረጃዎችም በምልከታና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ተሰብስበዋል ። በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተሰብስበው የተገኙ መረጃዎች በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዜዴ አማካኝነት ተተንትነዋል።

3.2.የናሙና አመራረጥ

3.2.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ

በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቢኖሩም ይህ ጥናት የተካሄደው በጢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነው።ከእነዚህ በወረዳው ከሚገኙት አራት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አጥኚው በጢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት እያገለገለ ስለሚገኝ ጥናቱን ለማጥናት ካለው ምቹነት አንጻር ጢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ብቻ በአመቺ ናሙና አማካኝነት ተመርጧል።

3.2.2 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ከተመረጠው ጢያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉት የክፍል ደረጃዎች ሁለት ሲሆኑ ሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ወሰኝ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁለቱም ክፍሎች ተመርጠዋል።

3.2.3 የመምህራን አመራረጥ

አጥኝው መምህራንን በመረጃ ምንጭነት የመረጠበት ምክንያት ደግሞ የጠቅላይ የንሞና ዘዴን መሰረት በማድረግ ነው። በትምህርት ቤቱ የሚገኙትን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ የጥናቱ አካላይ አድርጎ በማጠቃለል ነው።

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ ምልከታና ቃለ መጠይቅን የተጠቀመ ሲሆን ምልከታን በዋናነት ቃለ መጠይቅን ደግሞ በደጋፊ መረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጧል።

3.3.1 ምልከታ

በዚህ ጥናት በዋናነት አግልግሎት የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ ነው። የምልከታ ቅጾችን በማዘጋጀት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአካል በመገኘት አጥኝው ምልከታውን አካሂዷል።በዚህም መሰረት መምህራን በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለመመልከት ተችሏል።በምልከታው ጊዜም መረጃዎችን ለመያዝ እንያመቺ የምልከታ ቅጾችን በማዘጋጀት የመመዘኛ ደረጃዎች

3.3.2 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ተጠናክረዋል። የመረጃዎች ትክክለኛነትና የጥያቄዎቹን ተገቢነት በአጥኚው አማካሪ አማካኝነት ተገምግመው ለመምህራን ቀርበዋል።

3.4 የመረጃ ትንተና ዘዴ

በዚህ ጥናት በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከላይ በክለሳ ድርሳን በተገለጸው መሰረት በአይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ አማካኝነት አንድ በአንድ ተተንትነዋል።በመጨረሻም በታለሚ ትምህርት ቤት መማሪያ ክፍል ውስጥ ምልከታን መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ትንተናው ተካሂዷል።መረጃዎቹ እንደሚኖራቸው ይዘትና ዓላማ በገላጭ ስልት አማካኝነት ተተንትነው ተቀምጠዋል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር ከቃለ- መጠይቅና ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል። ትንተናውም የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ መተንተን የሚለውን የጥናቱን ዓላማ መሰረት ያደረገ ነው።

4.1 ከቃለ- መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር ከሚረዱ ብልሃቶች አኳያ

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶችን በመጠቀም ወይም ጥያቄ በመጠየቅ፣ በማብራራትና በመተርጎም፣ በመተንበይና በመገመት፣ በማጠቃለል፣ በጥልቀት ደግመው እንዲያነቡ በማድረግ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ የማነቃቂያ መንገዶችን በመፍጠር ትምህርቱን ታቀርባላችሁ?

መምህር 1፡- “ምንባቦችን ካስነበብኋቸው በኋላ ጥያቄ በመጠየቅ ሌሎች ምን ያህል እንዳነበቡት እመዝናለሁ። ስለዚህ መጠየቅ ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ ይረዳልና በትኩረት እጠቀምበታለሁ። እንዲሁም ያነበቡትን አሳጥረው እንዲፅፉት በማድረግ ማለትም የፃፉትን እንዲያነቡት፣ ያነበቡትን ደግሞ እንዲፅፉት ካደረግሁ በኋላ የይዘትና የስርዓተ ነጥብ ችግሮችን ለማረም የማጠቃለል ብልሃትን እጠቀማለሁ” ብለዋል።

መምህር 2፡- “የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር ብልሃቶችን አስቤውም ይሁን ሳላስበው እጠቀማለሁ። ምክንያቱም የክሂል ትምህርቱን በማቀርብበት ጊዜ ማብራራት፣ ለመጨረስ ስቃረብ ደግሞ ማጠቃለል የግድ ስለሆነ ነው። በይበልጥ ደግሞ ተማሪው ሙሉ ተሳታፊ መሆን አለበት ስለሚባል መልመጃዎችንና የሚሰሩ ጥያቄዎችን እየሰጡ በማሰራት ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃትን ለማዳበር እሞክራለሁ” ብለዋል።

መምህር 3፡- “ምንባቡ እየተነበበ እያለ መሃል ላይ በማቋረጥ የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በማቅረብ የመተንበይ፣ የማሰላሰልና የመገመት ብልሃትን ተጠቅሜ ካቀረብሁ በኋላ ከምንባቡ የተገነዘቡትን እንዲፅፉት እያደረግሁ ክሂሎችን በማቀናጀት ትምህርቱን ለማቅረብ እሞክራለሁ” ብለዋል።

መምህር 4፡- “ማንኛውም የንባብ ዘዴ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በማዳበር በኩል ሚናቸው ከፍተኛ ነው፤ ስለሆነም መጀመሪያ እንዲገምቱ እንድገምቱ ካደረኩኝ በኋላ ፤ መግቢያ በመስጠት ምሳሌውንና መነሻውን ተከትለው በጽሁፍ አብራርተው እንድያቀርቡ አደርጋለሁ። ይህን ካደረግሁ በኋላ እርማት በጽሁፍ እንዲሁም በቃል ገንቢ ሃሳቦችን በመስጠትና ምን ያህል ትምህርቱን እንደጨበጡት ጥያቄ በመጠየቅ እመዝናቸዋለሁ። በዚህ መልኩ የቋንቋ ትምህርት ብልሃቶችን እጠቀማለሁ” በሚል ገልፀውታል። መምህራን የማብራራትና መተርጎም፣ መተ

ንበይና መገመት፣ ጥያቄ የመጠየቅ እና የማጠቃለል ብልሃቶችን እየቀያየሩ ለመጠቀም እንደሚሞክሩ ነው ከቃለ መጠይቁ መረዳት የተቻለው። ማለትም ምንባብ ከማንበባቸው በፊት በመተንበይና በመገመት እንዲችሉ ማበረታታት ከዚያም ማስነበብ፣ ማብራራትና መተርጎም እንዲችሉ ማድረግ በመቀጠል ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ማሰራትና በመጨረሻ ትኩረት የሚደረጉባቸውን ነጥቦች በመለየትና ማጠቃለያ በመስጠት በሌላ ጊዜም በጥልቀት ደግመው እንዲያነቡ በማድረግ ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል።

4.1.2 አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ

1. ውጤታማና ሂደታዊ የመፃፍ ክሂል ትምህርትን እንደ ርዕሰ ጉዳዩ ለመጠቀም የምትወስኑበት መንገድ ምንድን ነው?

መምህር 1፡- “እኔ የማንበብና መፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሳስተምር የምጠቀመው የትምህርት ስልት ውጤት ተኮር ነው። ምክንያቱም የሚጠበቀውን ችሎታ ለማስገኘት ይረዳል ብዬ አስባለሁ። አቀላጥፈው ማንበብ እንዲችሉና የጽህፈት ችሎታን ለማዳበር ውጤት ተኮር በመሆኑ ነው።"

መምህር 2፡- “ተግባር ተኮር አቀራረብን እጠቀማለሁ። ምክንያቱም ራሳቸው አንብበው፣ የተገነዘቡትን ገልፀው፣ መፃፉ ማስተካከሉ ሁሉ የተማሪዎች ስራ በመሆኑ ተግባር ላይ ማተኮርን ይጠይቃል። ስለዚህ የማንበብ መፃፍ ክሂሎችን ሳስተምር ማሰራትን ስለሚጠይቅ ተግባሩ ላይ ትኩረቴን አደርጋለሁ” ብለዋል።

መምህር 3፡- “ውጤት ተኮር አቀራረብን መጠቀም የተሻለ ነው። ምክንያቱም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ስናስተምር ውጤት ለማስገኘት ነው። የሚፈለገው ውጤት እንዲመጣ ተግባር ላይ መሰረት አድርገን መስራት ይገባል” ብለዋል።

መምህር 4፡- “ይዘት ተኮር አቀራረብን መጠቀም ይገባል። ምክንያቱም የማንበብና መፃፍ ክሂሎች የሚነበበው ምንባብ ይዘት ላይ እና የሚፃፍበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ማተኮር የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው” በሚል ገልፀዋል።

ከመምህራን ቃለ- መጠይቅ መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ለማቅረብ አብዝተው የሚጠቀሙት ውጤት ተኮር የትምህርት አቀራረብን ነው። ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚጠቅም መሆኑን ያሳያል። አቀራረቦችን እየቀያየሩ መጠቀም የቋንቋ ትምህርቱን የተሻለ እንደሚያደርገው መገንዘብ አያዳግትም።

2. አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ሁል ጊዜ አቀናጅተው ያስተምራ ሉ? ወይስ ሁሌም በቅንጅት ነው እሚያሰተምሩት ?

መምህር 1፡- “አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር የትኛውን የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ልጠቀም የሚለውን ለመወሰን የትምህርቱ ይዘት ይጠቅማል። የትኛው ይዘት በምን አቀራረብ ይቅረብ፣ ምን ዓይነት ውጤት መምጣት አለበት የሚለውን ካሰብሁ በኋላ አቀራረብን እወስናለሁ” ብለዋል።

መምህር 2፡- “አስተማሪው፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የተማሪዎች ፍላጎት፣ የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ እና ሌሎችም አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች የሚቀርቡበትን አቀራረብ ለመወሰን ጠቀሚታ አላቸው። ምሳሌ አንድ የስነ ጽሁፍ ስራ ከዘውግ ስለሚመደብ በዘውጋዊ የትምህርት አቀራረብ ቢቀርብ ይመረጣል የሚል እምነት አለኝ” ብለዋል።

መምህር 3፡- “ይህ አንደ መምህሩ/ርቷ የማወሰን ምርጫ ይመስለኝል” ነው ያሉት።

መምህር 4፡- “የትምህርቱ ይዘት ስፋትና ጥበት፣ ሳቢነቱ፣ የተማሪ ፍላጎት ታሳቢ መደረግ አለባቸው” ብለዋል።

ከመምህራን ሃሳብ መመልከት እንደሚቻለው የትኛውን አቀራረብ ብሎ ለመወሰን የይዘቱ ስፋት ጥበቱ፣ ማስተማሪያ መጽሐፉ፣ የተማሪው ሁኔታ፣ የመምህሩ ምርጫ የሚሉት በዋናነት ተገልጸዋል። መምህሩ የይዘቱን አመችነት በማየት በየትኛው አቀራረብ መንገድ ማቅረብ እንዳለበት ሊወስን ይችላል። ነገር ግን አብዝቶተማሪዎች ምን እንደሚፈልጉና የትኛው አቀራረብ ሊመቻቸው እንደሚችል ማሰብ ሁሉ አቀራረቦችን ለመወሰን ይረዳል።

3. አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ተቀናጅተው እንዲቀርቡ መደረግ የሚኖርበት ጊዜ አለ ይላሉ? ወይስ ሁል ጊዜ የተቀናጁ ናቸው?

መምህር 1፡- “አዎ በተናጠልም ሊቀርቡ ይቻላሉ። ሆኖም ግን ተቀናጅተውም የሚቀርቡበት ጊዜ አለ። አንብቦ መረዳትን ሳስተምር ፅሀፈትን የሚጠይቅ ጉዳይ ይገጥመኛል ይህ ደግሞ የግድ ክሂሎች መቀናጀት እንዳለባቸው ያሳያል። ስዓት ለመቆጠብና በአንድ ጊዜ ሁለቱን ክሂሎች ለማሳደግ ስለሚያስችል ነው።”

መምህር 2፡- “አዎ! እየተቀናጀ የሚሰጡበት ጊዜ አለ። መቼ ነው ለሚለው ምንባቡ ከተነበበ በኋላ በተማሪዎች የሚሰሩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መፃፍን የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ የሚቀናጁበትም በተናጠል የሚሰጡበትም ጊዜ አለ” ብለዋል።

መምህር 3፡- “አዎ! ይዘቱ ማንበብና መፃፍን አስተሳስሮና አቀናጅቶ ሊያቀርባቸው ይችላል። ይህ ካልሆነ ግን መምህሩ በራሱ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን እያቀናጀ ሊያቀርብ ይችላል። ክሂሎች ለየብቻቸው ሊሰጡ ወይም ለተማሪዎች ሊቀርቡ እንደሚችሉ ግን መገንዘብ ያስፈልጋል”

መምህር 4፡- “ሁል ጊዜ የተቀናጁ ላይሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም ምንባቦች ከተነበቡ በኋላ ቃላዊ በሆነ መንገድ መልመጃዎች ሊሰሩ ችላሉ። ይህም አቀላጥፎ ማንበብን ብቻ ዓላማ ያደረገ ትምህርት ሊቀርብ የሚችል ስለሆነ ነው”።

4.1.3 አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማቅረብ አስፈላጊነቱን ለመፈተሽ ታስቦ ከተጠየቁት የተገኘ መረጃ ትንተና

1. የሁለቱ (አብብቦ መረዳትና የመፃፍ) ክሂሎች በቅንጅት መቅረብ ጥቅማቸው ወይም አስፈላጊነታቸው ምንድን ነው?

መምህር 1፡- “እነዚህ ክሂሎች በቅንጅት መቅረባቸው አንብቦ መረዳትንና መፃፍን ለማሳደግ ይጠቅማል። ምክንያቱም ማንበብ ሲኖር መፃፍ፣ መፃፍ ሲኖር ማንበብ ይኖራል። ስለዚህ ማንበብና መፃፍ ክሂሎች በተናጠል ከሚሰጡ ይልቅ በቅንጅት መሰጠታቸው ሁለት ችሎታ በአንድ ጊዜ ለማግኘት ይረዳል” ብለዋል።

መምህር 2፡- “በርካታ ጠቀሜታዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ አቀላጥፎ ለማንበብና ያነበቡትን ነገር እያስታወሱ ለመፃፍ፣ ሃሳብ በቀላሉ ለመረዳትና ላማደራጀት ይጠቅማል።”

መምህር 3፡- “አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል እውቀቶችን ለማስጨበት አስፈላጊ ነው። ሁለቱ ክሂሎች ላይ እውቀትና ችሎታ ለማግኘት ይጠቅማል” ብለዋል።

መምህር 4፡- “ዋናው አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር ጠቃሚ መሆኑ ነው” ብለዋል።

ከመምህራኑ ሃሳብ መገንዘብ እንደሚያስችለው አንብቦ የመረዳትንና መጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማቅረብ አስፈላጊ ነው። አንዱ ለሌላውን የሚገልጽ ስለሆነ ‹‹በአንድ ጠጠር ሁለት ወፎችን›› እንደመጣል ነው። በመሆኑም ለተማሪዎች ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ አንብቦ መረዳትና መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር ክሂሎች እየተቀናጁ እንዲማሩ መሆን አለበት የሚል አቅጣጫ ጥናቱ ያመላክታል።

2.ማንበብና መፃፍን በቅንጅት ሲያቀርቡ ዓላማቸውን አስቀድመው በመግለፅ ይጀምራሉ? ይህስ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ አካል ነው ይላሉ።

መምህር1፡-“አዎ! አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ዓላማ በመግለፅ እጀምራለሁ። ምክንያቱም አንድ ትምህርት ሲቀርብ ዓላማውን በማስተዋወቅ መጀመር ይገባል። ስለዚህ በቅንጅት የመቅረባቸውን ዓላማ መግለፅ የትምህርቱን ግብ ለማግኘት ስለሚያስችል የትምህርቱ አካል ነው” እላለሁ።

መምህር 2፡-“አዎ! ማንኛውም ትምህርት ሲቀርብ ዓላማ አለው። የግድ ደግሞ መገለፅ አለበት። ያ ካልሆነ የሚፈለገውን ውጤት ከትምህርቱ ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ ዓላማ መቅረፅና ዓላማቸውን መናገር አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች የበለጠ እንዲቀናጁ ያስችላል።”

መምህር3፡-“አዎ! ግን የሚነደፈው ዓላማ የክሂሎችን ቅንጅት የሚገልፅ መሆን አለበት። ሁለቱን ክሂሎች በማስተሳሰር የተዘጋጀ ዓላማ ትምህርቱን አጋፊ ስለሚያደርገው አንዱ አካል ነው።”

መምህር 4፡- “አዎ! አላማ የሚዘጋጀው ትምህርቱን ከሚጠበቀው ግብ እንዲያስገኝ ሆኖ ስለሆነ በቅንጅት የሚቀርቡትን አንብቦ መረዳትና መፃፍ ክሂሎች ለማጎልበት የሚጠቅም በመሆኑ የትምህርቱ አካል ነው።”

ሰፊውን መረጃ ከመምህራኑ ሃሳብ መመልከት ይቻላል። ሁል ጊዜም ግን አላማው ሳይገለጽ የሚጀመር ነገር የለም። በተለይም አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ከመቅረባቸው በፊት ለምን ዓላማ ትምህርቱ እንደሚቀርብ ለተማሪዎች ግልጽ በመሆነ መንገድ ተነግሯቸው መጀመር ያለበት መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል።

3. የማንበብ ክሂል ትምህርት ለመፃፍ ክሂል ትምህርት የሚፈጥረው እድል ካለ ቢገልፁት?

መምህር 1፡- “ማንበብ ካለ መፃፍ አለ። ማለትም ማንበብ ከቻሉ የመፃፍ ልምምድ ያደርጋሉ። ሃሳብ ይፈልቃል፤ ሙከራ ለማድረግ ይነሳሳሉ። ስለዚህ ማንበብ ለመፃፍ ክሂል መንገድ ሰጪ ነው።”

መምህር 2፡- “ዝም ብሎ አይፃፍም። ማንበብ መማር ይጠይቃል። የማንበብና የመረዳት ችሎታ ለመፃፍ በትንሹ ሃሳብን ለመግለፅ እድል ያመቻቻል። የሚፈጥረው እድል አለ።”

መምህር 3፡- “ከመጻፍ ማንበብ፣ ከመናገር ማዳመጥ ይቀድማል። ማለትም ሳነበብ አይጻፍም ተማሪዎች እንደመሆናቸው የማንበብና የመፃፍ ብቃታቸው ብዙም የጎለበተ አይደለም። ስለዚህ ማንበብ እንዲችሉ ማስተማር ያስፈልጋል። ይህ ጥረት ደግሞ ሃሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ያግዛቸዋል።”

መምህር 4፡- “ስለራስ መፃፍ የሚጀመረው ከማንበብ ነው። ማንበብ ካለ መፃፍ ሊኖር ይችላል።”

የመምህራኑ ሃሳብ እንዳለ ይሁንና ሁል ጊዜም የሚባለው ሃሳብ ማንበብ ካለ መጻፍ፣ መጻፍ ካለ ማንበብ ይኖራል፤ ማለትም እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው የሚለውን አጠንክሮ የሚያሳይ ነው። ስለሆነም አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎች ዘወትር በቅንጅት መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ይህ ጥናት ያረጋግጣል።

4.2 ከመምህራን ምልከታ የተገኘ ውጤት ትንተና

4.2.1 አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና

1. አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ወቅት የክሂል ትምህርት ደረጃዎችን ከእሳቤ ውስጥ በማስገባት ትምህርታቸውን ያቀርባሉ? ደረጃዎችን በቅደም ተከተል ያከናውናሉ?

መምህር 1፡- ቅድመ ንባብ እና ቅድመ ጽህፈት፣ የንባብ ጊዜ እና የጽህፈት ጊዜ ክንውን እንዲሁም ድህረ ንባብና ድህረ ጽህፈት ደረጃዎች አሉ። እነዚህን ደረጃዎች ቅደም ተከተል በማስጠበቅ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት አቅርበዋል። ማስረጃ የሚሆነውም ቅድመ ንባብ ተግባርን በማሰራበት ወቅት ስለቅድመ ጽህፈት እንዲያስቡ ወይም የገመቱትና ሃሳብ የሰጡበት ነገር ካለ በቢጋር መልክ እንዲነድፉት በማድረግ የቅድመ ንባብና ጽህፈት ተግባሮችን እንደሚያሰሩ መመልከት ተችሏል።

መምህር 2፡- የቅድመ፣ የንባብ/ ጽህፈት ጊዜ እና ድህረ ንባብ/ጽህፈት ክንውኖችን ካላለፈ የክሂሎች ትምህርት እንቅፋት እንደሚገኝጥም ከንግግራቸው መረዳት ተችሏል። ስለዚህ እነዚህን ደረጃዎች በሚያስተምሩበት ጊዜ ተጠቅመዋል። ዋናው ግን ደረጃዎችን ለተማሪዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ተናግረው ትምህርታቸውን ማቅረባቸውን መመልከት ተችሏል።

መምህር 3፡- “ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው መቅረብ እንደሳለባቸው ለተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ ትምህርቱን ሲያስጀምሩ አስተውያለሁ። ሲቀርቡም ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው መሆን አለበት ሲሉ በትምህርቱ ስዓት ማድመጥ ችያለሁ። እኔም የማቀርበው ቅድመ ንባብ/ጽህፈትን መጀመሪያ፣ የንባብ/ጽህፈት ጊዜን ለብቻ፣ የድህረ ንባብ/ጽኅፈትን ለብቻ እያደረጉ አቅርበዋል። ይህን ለማድረግ ግን የመማሪያ መፃህፍቱ የሚመራ በመሆኑ መጽሃፉን እየተመለከቱ ሲያቀርቡ ተመልክቻለሁል።”

መምህር 4፡- “አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ለማቅረብ የክሂል ትምህርት ደረጃዎች ያስፈልጋሉ። ያለነሱ ማቅረብ ከባድ ስለሆነ መጀመሪያ ቅድመ ተግባሮችን ስለሚጽፉት ነገር እንዲያስቡ ጊዜ በመስጠትና ስለምንባቡ እንዲገምቱ በማድረግ አስጀምረዋል። ምክንያቱም ደረጃዎችን ጠብቀው የሚቀርብ ተግባሮች ስላሉ ነው ሲሉ ማዳመጥ ተችሏል። ደረጃዎችን ሳይጠቀሙ ክሂሎችን አቀናጅተው አላቀረቡም። አንድ መምህር የአቀራረብ ደረጃዎችን መሰረት አድርጎ ማቅረብ እንዳለበት ጥናቱ ይጠቁማል።

መምህራን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ወቅት የክሂል ትምህርት ደረጃዎችን ከእሳቤ ውስጥ በማስገባት ትምህርታቸውን ያቀርባሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ተቀራራቢነት ያላቸውን መልሶች ሰጥተዋል። መልሶቻቸውን ከላይ መመልከት ስለሚቻል ልተወውና ክሂሎች ሲቀርቡ የአቀራረብ ደረጃዎች ይታሰባሉ። እነዙህ የቅድመ ንባብ/ጽህፈት፣ የንባብ/ጽህፈት ጊዜ እና ድህረ ንባብ/ጽህፈት ደረጃዎች ቅደም ተከተላቸውን እየጠበቁ መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ጥናቱ ያረጋግጣል። ያለነዚህ ደረጃዎች የክሂል ትምህርቶች መቅረብ ስለማይችሉ ትኩረት መስጠት፣ የተሻለ ውጤት ለማግኘት ያስችላል።

4.2.2 አንብቦ ስለመረዳትና ስለመፃፍ ክሂል አካታችነት የተገኘ መረጃ ትንተና

የቀረበው ርዕስ አንብቦ የመረዳትንና የመፃፍ ክሂልን ለመማር ይጋብዛል?

መምህር 1፡- “ብዙውን ጊዜ የሚጋብዝ እንደሆነ አሳይተዋል። ጽህፈትን የሚመለከቱ ተግባሮች የማንበብ ክሂል ትምህርት መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ላይ ስለሚያቀርብ እነዚያን ተግባሮች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ሲያሰሩ ተመልክቻለሁ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በቃል ብቻ የአንብቦ መረዳት ተግባሩ ስለሚከናወን ሁል ጊዜ ነው ማለት አይቻልም እንዳልሆነ ጥናቱ ይጠቁማል።

መምህር 2፡- ከቀረበው ርዕስ አንጻር ሁሉቱም ክሂሎች በቅንጅት እንደቀረበ በተሰጠው የክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መረዳት ተችሏል።

መምህር 3፡-“አዎ! ሁል ጊዜም ቢያንስ ካነበቡት ምንባብ የተገነዘቡትን እንዲጽፉ ስለሚታዘዙ እና መምህሩም እንዲጽፉ ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ። ጥናቱም አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂሎች ሁልጊዜ ባይሆንም በቅንጅት ባለመቅረባቸው አንዱ ማሳያ መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል።

መምህር 4፡- “ከመምህሩ መመልከት እንደተቻለው መጽሃፉ ጋባዥ እንዳሆነ ነው፤ ነገር ግን አስተማሪ መምህሩ በራሳቸው መንገድ አቀናጅቶ ለማቅረብ ሲሞክሩ ተስተውሏል። አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ

የመጻፍ ክሂልን ማሰብ ይጠበቃል። ስላነበቡት ነገር በቃል ከሚገልጹ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በጽሁፍ እንዲገልጹት በማድረግ ሁለቱን ክሂሎች በቅንጅት ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ማየት ችያለሁ።”

መምህራን አንብቦ የመረዳት ትምህርቱ የይዘት አቀራረብ፣ የመፃፍ ክሂልን የሚያካትት መሆኑና አለመሆኑን ተጠይቀው የሰጡት ሃሳብ የተለያየ መሆኑን ከላይ ከቀረቡት መገንዘብ ይቻላል። ዋናው ግን ምንባቦች የመጻፍ ተግባርን ሊያካትቱ ወይም ላያካትቱ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን አካታች መሆን እንዳለባቸው ይህ ጥናት ይጠቁማል። ምክንያቱም አንድን ክሂል ብቻ ነጥሎ ከማስተማር እያጣመሩ ወይም እያቀናጁ ማስተማር የአስተሳሰብ አድማስን፣ የቋቋ ችሎታንና ማህበራዊ ተግባቦትን ስለሚፈጥር ነው።

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ የቀረቡበት የአቀራረብ ስልት ምን ይመስላል?

መምህር 1፡- አስነብበው በማጻፍ፣ አጽፈው በማስነበብ የተሳሰረ ተግባር በመሰራት የሚያቀርቡበትን በመቀያየር ለማቅረብ ጥረት አድርገዋል።

መምህር 2፡- የተማሪዎችን ስህተቶች በመልቀምና ሰሌዳ ላይ እየጻፉ በማሳየት እንዳይደገሙ በማስጠንቀቅ

መምህር 3፡- እርስ በርስ እንዲተያዩና አንዱ የሌላውን በመተያየት ለማስተካከል አሻሽሎ ለማንበብና አሻሽሎ ለመጻፍ እንዲተራረሙ በማድረግ ስያስተምሩ ተመልክቻለሁ፤ ይህም ሊሆን የሚችል ስልት ስለሆነ የሚበረታታ ነው።

መምህር 4፡- ከማንበብና ከመጻፋቸው ቀደም በማለት እንዴት ማንበብና መጻፍ እንዳለባቸው እንዲያስቡ ካደረጉ በኋላ በማስነበብ፣ ያለመደናቀፍ አንብቦ በማሳየት፣ መልመጃዎችን በማሰራት መልሶ በምዘና ስልት በመጠየቅ ሲያስተምሩ ተመልክቻለሁ።

ከመምህራን ምልከታ እንደተገኘው መምህራን የተለያዩ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ ነው። በእርግጥ አንድን ስልት አዘቅትሮ መጠቀም አሰልችነትን ስለሚያመጣና ይህንን ስልት ብቻ ተጠቀም የሚለው ስለሌለ የማስተማሪያ ስልቶችን እየቀያየሩ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ይህ ጥናት ያመላክታል። ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸውም ያደርጋል። ስለዚህ መምህራን አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ሲያስተምሩ በየትኛው ስልት ማቅረብ እንዳለባቸው ወስነው መቅረብ አለባቸው።

መምህራን የይዘትና ተግባር ተኮር አቀራረብ ዘዴዎችን መሰረት አድርገው ትምህርቱን አቅርበውታል? ወይስ ለአንዱ ስነ- ዘዴ ትኩረት ሰጥተዋል?

መምህር 1፡- ለተግባር ተኮር ስነ ዘዴ ትኩረት ሲሰጡ ተስተውለዋል። ተማሪዎች በራሳቸው እንዲሞክሩ ወይም እንዲጥሩ በማበረታታትና በመቀስቀስ የተሻለ ሲያግዟቸው በተደረገው ምልከታ ማየት ተችሏል።

መምህር 2፡- ተማሪዎች ይዘቱ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሞክሩ ይዘት ተኮር አቀራረብን ብቻ ተጠቅመው ትምህርቱን ሲያቀርቡ መመለተከት ተችሏል።

መምህር 3፡- ለይዘት ተኮር አቀራረብ ትኩረት ሲሰጡ መመልከት አልተቻለም። ይሁን እንጂ ተማሪዎችን በተግባር አሰማርተው በራሳቸው እንዲሞክሩ ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ።

መምህር 4፡- የማስተማሪያ ዘዴዎችንና የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦችን ለይቶ የመጠቀም ችግር ማስተዋል ተችሏል። መምህሩ ለተማሪ ተኮር ማስተማር ስነ- ዘዴ እንጂ ለይዘት ተኮር አቀራረብ ትኩረት በመስጠት ሲያስተምሩ ምልከታው ላይ አልተስተዋለም።

ከላይ የቀረበላቸውን ጥያቄ በተመለከተ መምህራን የተለያዩ አቀራረብ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ይታወቃል። ዘወትራዊ ከሆነ አጠቃቀም ግን መውጣትና አቀራረቦችን እየለዋወጡ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ይህ ጥናት ያሳያል።

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ ወይም አንዱ ክሂል ከሌላው ጋር የሚኖረውን ትስስር ለተማሪዎች ነግረዋቸዋል?

መምህር 1፡- ነግረዋል! ለመጻፍ ማንበብ እንዳለ ገልፀዋል።

መምህር 2፡- አልነገሩም! በቀጥታ የትምህርቱን ዓላማና ጠቀሜታ ሳይገልጡ ነው ትምህርቱን የጀመሩት። መምህሩ ትምህርቱ የሚያስገኘውን ዓላማና ጠቀሜታ ማስተዋወቅ እንዳለባቸው መመልከት ችያለሁ።

መምህር 3፡- ነግረዋል! ማንበብ መጻፍንይቀድማል፤ ለመጻፍ ማንበብ ስለሚያስፈል ነው ሲል በምልከታ ወቅቱ የተገኘ ሃሳብ ነው።

መምህር 4፡- ነግረዋል! ዓላማዎችንና የክሂሎችን ትስስር ሲገልጹ ብዙ ጊዜ መውሰዳቸው ነው እንጂ የገለጹበት መንገድ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ትስስር በሚገባ ያሳየ ነው።

የመምህራን ሃሳብ እንደሚያሳየው አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን ጠቀሜታ በሚገባ ለተማሪዎች የማይናገሩት በዝተው መመልከት ስለተቻለ ትምህርቱ ላይ ችግር ያለ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ያስችላል። ስለዚህም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማቅረብ ጠቀሜታ ለተማሪዎቻቸው መግለጽ እንደሚገባ ጥናቱ ያረጋግጣል።

በዕለቱ የቀረበውን ይዘት አንብበው እንዲፅፉ ወይም የጽሑፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ እንዲያነቡት ይደረጋል?

መምህር 1፡- በተደረገው ምልከታ አንብቦ መረዳት ክሂልን ሲያስተምሩ በቃላቸው የማሰራት ልምድ ጎልቶ ታይቷል።

መምህር 2፡- ቅድመ ንባብን በቃላቸው ካሰሩና ምንባቡን በተደጋጋሚ ካስነበቡ በኋላ አሳጥረው እንዲጽፉ በማድረግ ክፍል ውስጥ የጻፉትን ሲያስነብቧቸው ተስተውሏል።

መምህር 3፡- በተደረገው ተደጋጋሚ ምልከታ ደጋግመው ሲያስነብቡ ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ ስለሚጠናቀቅ የጽሁፍ ልምምዱ እንደተጀመረ ሳይጠናቀቅ የሚቀርበትን ሁኔታ መመልከት ተችሏል።

መምህር 4፡- አንብቦ መረዳት ትምህርቱ ከቀረበ በኋላ የጽሁፍ ልምምዱ እዛው ክፍል ውስጥ ለተወሰነ ደቂቃ ለማከናወን ጥረት ሲደረግ ተመልክቻለሁ።

ከምልከታው እንደተገኙት መረጃዎች ምህራን አንብቦ መረዳትን ካስተማሩ በኋላ የጽህፈት ልምምድ ተግባሩን ለማከናወን ሲጥሩ የታየ ቢሆንም አንብቦ መረዳትና መጻፍ ክሂሎችን በአንድ ላይ አቀናክተው ለማስተማር ጊዜን በሚገባ መከፋፈል ያስፈልጋል። ምክንያቱም በርካታ ስራዎችን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። ስለሆነም መምህራን የመጀመሪያው ቀን አስነብበዋቸው ከሆነ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ በአንብቦ መረዳቱ ርዕስ የጽህፈት ልምምድ በማድረግ ክሂሎችን እያቀናጁ ማስተማር እንደሚቻል ወይንም አንባቢ ተማሪዎችን በመወሰን ለመጻፍ ልምምድ ተግባር ስዓቱ የበቃ እንዲሆን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ትምህርት የቋንቋ ብቃት ችሎታቸውን ለማሳደግና በቀላሉ የተቀላጠፈ ተግባቦት የሚያጎለብት መሆኑን ያስገነዝቧቸዋል?

መምህር 1፡- አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ብቃትና ችሎታ መዳበር ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማርና ለመተግበርም ሚና ከፍተኛ ሰለሆነ ሁሌም የምተገብረው ነው።

መምህር 2፡- በግልጽ ብቃታቸውን ለማሳደግ እንደሚማሩት አልተናገሩም። ምንባቦችን እያነበቡ ካሳዩ በኋላ እንዲያነቡ ያደርጋሉ እንጂ በእርግጥ ይህ መሆኑ ብቃታቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳ መገንዘብ የሚያስችል ነው። ነገር ግን በግልጽ መነገር አለበት።

መምህር 3፡- በተደረገው ተከታታይ ምልከታ ክሂላቸውን ለማሳደግና ለተቀላጠፈ ተግባቦት እንደሚረዳ አልገለጹም። በቀጥታ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ቅንጅታዊ ሲያቀርቡ ወይም ትምህርቱን ሲሰጡ የእለቱን

ምንባብ አስነብበውና የጽሀፈት ልምምድ አድርገው ትምህርታቸውን በማጠቃለል ሲያጠናቅቁ ነው ማስተዋል የተቻለው።

መምህር 4፡- በትክክል ተናግረው አስጀምረዋል።

የመምህራን ሃሳብ የሚያሳየው አንዳንዱ በትክክል ተግባቦትንና የቋንቋ ብቃት ችሎታን እንደሚያጎናጽፍ ሲገልጹ ጭራሽ የሚያስገኘውን ጥቅም ሳይገልጹ የሚጀምሩ እንዳሉ መመልከት ተችሏል። በዚህ መሰረት ጥናቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ የተቀላጠፈ ተግባቦትና የቋንቋ ብቃት ችሎታ የሚያስገኙ መሆኑን ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊትና በኋላ እየደጋገሙ በመግለጽ ብቃታቸውን ለማግኘት እንዲችሉ ማበረታታት የሚጠበቅ መሆኑን ማስገንዘብ መቻል አለባቸው የሚል አመላካች ሃሳብ ጥናቱ ያቀርባል።

ሁልጊዜም የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ከማቅረባቸው በፊት ዓላማቸውን በማስተዋወቅ ይጀምራሉ?

መምህር 1፡- የክሂል ትምህርቶችን አላማና ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብን አስፈላጊነት በመግለጽ አቅርበዋል። ከትምህርቱም አቀላጥፎ የማንበብ ብቃትና በሚፈልጉት ርዕሰ ጉዳይ መነሻነት ለመጻፍ ትምህርቱ እንደሚያስችል ሲገልጹ መመልከት ተችሏል።

መምህር 2፡- በቀጥታ ትምህርቱን አቀረቡ እንጂ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማቅረብ አላማቸውን መግለጽ አልቻሉም።

መምህር 3፡- ክሂሎቹ በቅንጅት የሚቀርቡበትን ዓላማ አልገለፁም።

መምህር 4፡- ዓላማቸውን የዕለታዊ እቅዳቸው ላይ የገለጹት ቢሆንም ክፍል ውስጥ ግን ለተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማ በማስተዋወቅ ሳይሆን በቀጥታ ወደ ትምህርቱ በመግባት ጀምረዋል።

ከመምህራን ሃሳብ መመልከት እንደሚቻለው ብዙውን ጊዜ መምህራን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማቅረብ ዓላማቸውን በግልጽ ለተማሪዎቻቸው ሳያሳውቁ ወይንም ሳይናገሩ ትምህርቱን በቀጥታ እንደሚያቀርቡ ነው። ይህ መሆኑ ተማሪዎች ትምህርቱ የሚቀርብበትን ዓላማ እንዳይገነዘቡት ያደርጋል። ስለዚህ ለምን ዓይነት ዓላማ እንደሚማሩ ማወቅ ስለሚኖርባቸው ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ የተቀረፀላቸው ዓላማ ለተማሪዎች መሰጠት ያለበት መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል።

ክሂሎችን በቅንጅት ሲያቀርቡ ውጤታማ ወይም ሂደታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦችን እየቀያየሩ እንደአስፈላጊነታቸው ይገለገላሉ?

መምህር 1፡- ብዙውን ጊዜ የምጠቀመው ውጤታማ (ውጤት ተኮር) አቀራረብን ሲጠቀሙ በምልከታው ማስተዋል ተችሏል። ክሂሎችን በቅንጅት ማቅረብ የማንበብና መጻፍ ችሎታን ለማሳደግ ስለሚጠቅም ነው።

መምህር 2፡- ምንባቡ ረዘም ያለ ከሆነ ሂደታዊ አቀራረብን እጠቀማለሁ። አጭርና ብዙም ያልረዘሙ ከሆኑ ግን ውጤት ተኮር አቀራረብን በመጠቀም በቅንጅት የሚቀርቡትን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ ተመልክቻለሁ።

መምህር 3፡- ውጤት ተኮርን ብቻ ተጠቅመዋል።

መምህር 4፡- ለቋንቋ ትምህርቱ ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮርና ዘውግ ተኮር አቀራረቦችን እጠቀማለሁ። ክሂሎችን በቅንጅት ሳስተምር ግን ውጤት ተኮር አቀራረብን ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ ማስተዋል ተችሏል።

መምህራኑ በብዛት አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ ውጤት ተኮር አቀራረብን እንደሚጠቀሙ መመልከት የተቻለ ሲሆን ሌሎችን የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦች ትኩረት ሲሰጡ አልተስተዋለም። አዘውትረው አንድን አቀራረብ ከመጠቀም ይልቅ ሌሎችን አቀራረቦች እየቀያየሩ መጠቀም ለትምህርቱ ስኬታማነት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው መገንዘብ የሚያስፈልግ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። በመሆኑም መምህራን ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮርና ዘውግ ተኮር የትምህርት አቀራረቦችን ትኩረት መስጠት አለባቸው የሚል ማሳያ አስቀምጧል።

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ካቀረቡ በኋላ ማጠቃለያ የሰጡበት መንገድ ምን ይመስላል?

መምህር 1፡- ከጻፉት ውስጥ የተሻሉ ጽሁፎችን በመምረጥ ለአብነት ወስዶ እንዴት ጽሁፎች መዘጋጀት እንዳለባቸውና ጽሁፎችን በማስነበብ በምን መልኩ ማንበብ እንዳለባቸው አንብቦ በማሳየት ማጠቃለያ ሰጥተዋል።

መምህር 2፡- ከምንባቦች የተረዱትን በአንድ ወይም ሁለት መስመር እንዲጽፉ በማድረግ ማጠቃለያ ሰጥተዋል።

መምህር 3፡- ስዓት ተይዞላቸው በፍጥነት አቀላጥፈው እንዲያነቡና ስለሆነ ነገር እንዲጽፉ በማድረግ የራሳቸውን ሃሳብ ጨምረው አጠቃለዋል።

መምህር 4፡- የትምህርቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ጠይቀው ማጠቃለያ ሰጥተዋል።

መምህራን የየራሳቸውን መንገዶች እየተጠቀሙ ማጠቃለያዎችን ይሰጣሉ፤ የሚሰጧቸው ማጠቃለያዎችም ክሂሎች በቅንጅት የሚቀርቡ መሆናቸውን ያሳያሉ። ነገር ግን መምህራን አጭር ጽሁፎችን አዘጋጅተው በመቅረብ አቀላጥፈው እያነበቡ በማሳየትና በራሳቸው የተጻፉ ጽሁፎችን በማንበብ ማሳየት፣ እንዲሆም በጋራ የመጻፍ ሂደትን ተግባር ላይ በማዋል ቢጠቀሙበት የሚል የጥቆማ ሃሳብ ጥናቱ ያቀርባል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳብ

በዚህ ክፍል አጠቃላይ በጥናቱ የታዩ ፍሬ ነገሮችን በአጭሩ ዳሰሳ ከተደረገባቸው በኋላ እነዚህን የማጠቃለያ ነጥቦች መሰረት በማድረግ የመፍትሔ ሀሳቦችም ተቀምጠውበታል።አጥኝው በመጀመሪያው ምዕራፍ በጥናቱ የተነሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በእያንዳንዱ ነጥቦች ውስጥ ነታዩ ችግሮችና ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች በማስቀመጥ አጠቃሏል።

5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አቢይ ዓላማው በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል መምህራን ትኩረቱን በማድረግ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ መተንተን ነው።

የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች

1.አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን በሚያዳብር መልኩ መቅረቡን መመርመር ፣

2.በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚከሰቱ የክፍል ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ መለየት ናቸው።

።።በቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ተግባርን በቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች አማካኝነት እንደሚከናወን ይታወቃል። ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክሂሎችን በክፍል ውስጥም ሆነ በተለያዩ የትምህርት ማሰራጫ ስፍራዎች ሲያስተምሩ የክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ በሚገባ ማወቅና መተግበር አስፈላጊ ነው።

።።የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በዓመታዊ ውም ሆነ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸው የቋንቋ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብ ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቃል።

።።የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ቅንጅታዊ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ለማንኛውም ተማሪ ግልጽ መሆን ይገባል።

።።አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍን ክሂሎችን አቀናጅቶ መስጠት ግን የሁለት ክሂሎችን ችሎታ ለመጎናጸፍ ያግዛል የሚለውን ዋና ሃሳብ መገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት እንደሚጠይቅ ጥናቱ ያሳያል። በመሆኑም ለተማሪዎች ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ አንብቦ መረዳትና መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር

ክሂሎች እየተቀናጁ እንዲማሩ መሆን አለበት የሚል አቅጣጫ ጥናቱ አስቀምቷል። እንዲሁም የማስተማሪያ ስልቶችን እየቀያየሩ መጠቀም ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ እንደሆነ ጥናቱ አረጋግጧል። ስለዚህ መምህራን አንብቦ የመረዳትና መጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ሲያስተምሩ በየትኛው ስልት ማቅረብ እንዳለባቸው ወስነው መቅረብ አለባቸው።

። አጥኚው ምልከታ ባደረጉባቸው ክፍሎች ባገኘው መረጃ መሰረት መምህራን የማብራራትና መተርጎም ፣ መተንበይና መገመት ፣ጥያቄ የመጠየቅና የማጠቃለል ብልሃቶችን እየቀያየሩ ለመጠቀም እንደሚሞክሩ ነው።

።መምህራን የየራሳቸውን መንገድ እየተጠቀሙ ማጠቃለያዎችን ይሰጣሉ። የሚሰጧቸው ማጠቃለያዎችም ክሂሎችም በቅንጅት የሚቀርቡ መሆናቸውን ያሳያሉ።

። መምህራን አጫጭር ጽሁፎችን አዘጋጅተው በመቅረብ አቀላጥፈው እያነበቡ በማሳየትና በራሳቸው የተጻፉ ጽሁፎችን በማንበብ ማሳየት፣ በጋራ የመጻፍ ሂደትን ተግባር ላይ በማዋል ቢጠቀሙበት የሚል የጥቆማ ሃሳብ ጥናቱ ያቀርባል ።

5.2 የመፍትሔ ሃሳብ

ከጥናቱ ማጠቃለያ በመነሳትም የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሳቦች ማቅረብ ተችሏል።

መምህራን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር በዕለታዊ የትምህርት እቅዳቸው ቢተገብሩት፣

መምህራን የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት መሰረት ያደረጉ አጫጭር ርዕሶችን ለተማሪዎቻቸው ቢያቀርቡ፣

መምህራን ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ በጋራ አንብበው የተረዱት በጽሁፍ ለማብራራት የሚመቹ ጽሁፎች እያዘጋጁ ቢያቀርቡ፣

መምህራን ለተማሪዎች ስሜት ሳቢ የሆኑ ጽሁፎች በማንበብ ማነሳሳት ቢችሉ፣

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ የስነ የጽሁፍ አይነቶችን በመጠቆም አንባቢ ትውልድ ቢፈጥሩ፣

መምህራን ተማሪዎችን በስነ ጽሁፍ ክበባት በንቃት በመሳተፍ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማዳበር እንድችሉ ቢያበረታቱ፣

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን የተለያዩ መጻህፍትን አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ ክፍል ውስጥ እንድያነቡ ቢያደርጉ ፣

ዋቢ መጽሐፍት

ተስፋዬ ሽዋዬ።(1981)። (1981) ።“ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር።።” አዳስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ታረቀኝ አይሶ። (2013)። “አንብቦ የመረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂልቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ” ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)።

እመቤት እሸቴ። (2011) ። “አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና” ("በ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኪሪነት) ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)።

ያለውእንዳወቀያለው ።(2001)።የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ።(ሁለተኛ ዕትም) አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጌታቸው ቸርነት። (2001)። “በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት” ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሑፍ ትምህርት ክፍል። (ያልታተመ)።

..... .,(1990). Reading in the Class room. London: Macmillan Publishers Ltd.

..... (2001). Curriculum development in teaching. Cambridge: Cambridge University press.

..... (1993). "First and Second language reading proficiency of year 3,4 & 6 Children in Malaawi and Zambia" Journal of reading in a foreign language.

Atkin S,J.etal. (1996). Skills development methodology part two Addis Ababa: Addis Ababa University press .

Block, Cathycolling. (1997). Teaching the Language arts.Expanding thinking Students Centered instraction. Bastone: Allyn and Bacon.

Block,Cand Mangier, J. (1995). Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature, Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion.

Brwon,J.D. (1994). Princple of Language Learning and Teaching.New Jersey: Profice Mull Regent.

Byrne,D. (1981). Integration Skill in Johnson and Marrow. Hongkong: Long man Group Ltd.

Celce-Murcia, M.(eds.) (1991). Teaching English as a Second or Foreign 96 Language.(2nd ed.). Boston:Heinl & Heinle publishers.Ltd.

Conely,M,W, (1997). Content Reading Instruction.Communication.Approach New York: Mc Graw-Hill lnc.

Cunnings worth, A. (1984). Evaluating and selecting EFL Teaching Materials. London: Heinemann Educational Books.

Doff A (1988). Teaching Engllish, Atraining course for cl Teachers. Cambridge. Cambridge University press.

Durkin,D.(1997). Teaching them to read. (5th edition) Boston: Allyn and Baconlnc.

Gary,Cobine.(1995).Writing as aresponse to reading. (http:// www.vatide.com./pnp/ERIC/write-read.htm.

Gilbert,J.(1982). Clear Speech: Pronuciation and Listening Comprehension in English.Tesol Quarterly.

Grant N.(1982). Making the Most of Your Text Book. London: Longman Group Ltd.

Grellet, F. (1981). Developing reading skills. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, J. (1991). Teaching the practices of English Language.London Long man.

Harp, Bill and Brewry, John. (1996). Reading and Writing Teaching for the connection.(2nd Ed.) S.A: Har court brace and campany.

J.C.Richards and T.S. Rodgers. (1986). Approaches and methods in language teaching.(Low Price Edition) London, Cambridge University Press.

Leki, L. (1996). Coaching from the marging, Issuesin Written Response B.kroll/ Second Ed / anfuage Written, Research IN sights for the class room. Cambridge, Cambridge university press.

Lindsay and Knight. (2006). Learning and teaching English: A course for teachers. Oxford: Oxford university press.

Lindsay.(2006). Teaching and Learning English. Oxford: Oxford University Press.

Littile Wood, W.(1981) Communcative language teaching.Cambridge: Cambridge University press.

May, Frank. B. (1990). Reading as communication.New York: Macmilan Publishing Company.

McDonough, J. ana Shaw, C. (1992). Intetegrated Skills in ELYA Teachers Guide. Oxford: Black well.

Nuttall, C. (1982). Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London. Heinemann Educational books. Nunan D. (1988). Syllabus Design. Oxford: Oxford university press.

Oxford, R. (2001). Integrated Skills in the ELS/EFL Class room ERTV. Maio:eric@Cas.org

Raimes, A. (1983). Techniques in teaching writing. Oxford: Oxford University press Inc.

Richards, J. C. (1990). The language teaching matrix. Cambridge: Cambridge University press.

Rivers, W. (1981). Teaching Foreign Language Skills. Chicago: Chicago University press.

Ruddel, Martha Rapp. (1997). Teaching content Reading and Writing. (2nd ed.).U.A.S: Allyn and Bacon.

Silva, T. (1990). Towards understanding writing. The ESL.resarch and its implication.Joumal of second language writing.

Ur.P. (2006). A course in language Teaching practice and Theory. 13th Printing Cambridge: Cambridge University.

Wallace, C. (1992).Language teaching in Reading. New York. Oxford university press.

Widdowson, H.G.(1976). Teaching Language as Communication.Oxford: longman group.

Williams, E. (1984). Reading in the Language Class room. London: MacMillan publishers Ltd.

አባሪ አንድ፡- የመምህራን ቃለ_መጠይቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ሰብዓዊነት ኮሌጂ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ_ምረቃ መርሃ ግብር

ለጢያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ_መጠይቅ

ውድ መምህራን፡- ይህ ጥናት አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ በጢያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ክፍል መምህራን ተተኪሪነት በሚል ርዕስ በመዘጋጀት ላይ ያለ ምርምር ነው። ለዚህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ድርሻችሁ ከፍተኛ በመሆኑ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ እንድታደርጉ ትጠየቃላችሁ። ለምታደርጉልኝ እገዛ አመሰግናለሁ።

ሀ. የትምህርት ቤቱ ስም ..... ለ. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን ..... ስዓት .....

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶችን በመጠቀም ወይም ጥያቄ በመጠየቅ፣ በማትራራትና በመተርጎም፣ በመተንበይና በመገመት፣ በማጠቃለል፣ በጥልቀት ደግመው

እንዲያነቡ በማድረግ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ የማነቃቂያ መንገቦችን በመፍጠር ትምህርቱን ታቀርባላችሁ?

ውጤታማና ሂደታዊ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦችን እንደርዕሰ ጉዳዩ ወይም ይዘቱ ለመጠቀም የምትወስኑበት መንገድ ምንድን ነው? ከእነዚህ አቀራረቦች ውጪ የምትጠቀሙት አቀራረብ ይኖራል?

አንብቦ የመረዳት የመፃፍ ክሂሎች ተቀናጅተው እንዲቀርቡ መደረግ የሚኖርበት ጊዜ አለ ይላሉ? ወይስ ሁል ጊዜ የተቀናጁ ናቸው?

የሁለቱ ክሂሎች በቅንጅት መቅረብ ጥቅማቸው ወይም አስፈላጊነታቸው ምንድን ነው?

ሁለቱ ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ ዓላማቸውን አስቀድመው በመግለፅ ይጀምራሉ? ይህስ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ አካል ነው ይላሉ?

የማንበብ ክሂል ትምህርት ለመፃፍ ክሂል ትምህርት የሚፈጥረው እድል ካለ ቢገልፁት?

አባሪ ሁለት፡- መምህራንን ምልከታ ማድረጊያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ሰብዓዊነት ኮሌጂ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ_ግብር

ለሶዶ ወረዳ ለሚገኙ ታላሚ ጤያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና በሚመለከት የክፍል ውስጥ ምልከታ፡-ውድ መምህራን፡-

ሀ.የትምህርት ቤቱ ስም .....ለ. ምልከታው የተደረገለት መምህር ስም ..... ክፍልና ሴክሽን.....ሐ. የምልከታው ስዓት..... መ.የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ .....

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ወቅት የክሂል ትምህርት ደረጃዎችን ከእሳቤ ውስጥ በማስገባት ትምህርታቸውን ያቀርባሉ? ደረጃዎች ስለሚለያዩ እንዴት አጣጥመው አቅርበዋል?

አንብቦ የመረዳት ትምህርቱ ይዘት አቀራረብ የመፃፍ ክሂልን ለመማር ይጋብዛለል?

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ የቀረቡበት የአቀራረብ ስልት ምን ይመስላል?

መምህራን የይዘትና ተግባር ተኮር አቀራረብ ዘዴዎችን መሰረት አድርገው ትምህርቱን አቅርበውታል? ወይስ ለአንዱ ስነ- ዘዴ ትኩረት ሰጥተዋል?

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ ወይም አንዱ ክሂል ከሌላው ጋር የሚኖረውን ትስስር ለተማሪዎች ነግረዋቸዋል?

በዕለቱ የቀረበውን ይዘት አንብበው እንዲፅፉ ወይም የጽሑፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ እንዲያነቡት ይደረጋል?

አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል ትምህርት የቋንቋ ብቃት ችሎታቸውን ለማሳደግና በቀላሉ የተቀላጠፈ ተግባቦት የሚያጎለብት መሆኑን ያስገነዝቧቸዋል?

ሁልጊዜም የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ከማቅረባቸው በፊት ዓላማቸውን በማስተዋወቅ ይጀምራሉ?

ክሂሎችን በቅንጅት ሲያቀርቡ ውጤታማ ወይም ሂደታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦችን እየቀያየሩ እንደአስፈላጊነታቸው ይገለገላሉ?

የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ካቀረቡ በኋላ ማጠቃለያ የሰጡበት መንገድ ምን ይመስላል?

አባሪ ሶስት ፦የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር

"የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና በሚል ርዕስ ለሚሰራው ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጪያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9 ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ሲያስተምሩ ክፍል ውስጥ በመገኘት የተወሰደ ምስልና የተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ውጤት

ምስል አንድ ፡




ምስል ሁለት




ምስል ሶስት



ጽሁፍ አንድ፡-




ጽሁፍ ሁለት፡-



:-

ጽሁፍ ሶስት



[i]